# ኢትዮ ቻምበር

ሚዲያ ጭማቂ

**በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት**

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኮሚኒኬሽንና ህዝብ ግንኙኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ ወርሃዊ የሚድያ ጭማቂ

መጋቢት 2014 ዓ.ም.

የኢትዮ-ቱርክ የንግድና...2

ምግብ የሚያቀነባብሩ 28...2

የአገር ውስጥና የተለያዩ...2

የግብር ከፋይ ቅሬታዎችን...2

የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዋጋ...3

መንግሥት እጁን የታሰረበት...3

ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ...4

የሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ...5

የአበባ ምርት የመላኪያ...6

የነዳጅ ስርጭት ችግር...6

የባንኮች ብድር አሰጣጥን...6

የምግብ ዘይት የፋብሪካ...7

በኦጋዴን የተፈጥሮ ነዳጅ...7

ከጂኦተርማል የኤሌክትሪክ ኃይል...8

በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾችን...8

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዘካ...9

ዘመን ባንክ የማስተር ካርድ...9

የግል አየር መንገዶች አድሎ...10

የኢትዮጵያ አየር መንገድ...10

የጭነት አግልግሎትን ያቀላጥፋል...10

## ምክር ቤቱ ያዘጋጀውን ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎት በይፋ አስጀመረ








የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከየአይርላንድ መንግስት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በትሬድ ማርክ ኢስት አፍሪካ (Trade Mark East Africa) የቴክኒክ እገዛ አማካኝነት ያዘጋጀውን ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎት መጋቢት 28 ቀን 2014ዓ.ም በራዲሰን ብሉ ሆቴል በይፋ አስጀመረ፡፡

ምክር ቤቱ እስካሁን ሲሰጣቸው የነበሩትን አገልግሎቶች በኦንላይን ለመስጠት በዋነኛነት አባላትን ለመመዝገብ የሚያስችል የአባላቶች የመረጃ ቋት፣ የአቻ ለአቻ የቢዝነስ ትስስር (B2B) መፍጠር፣ ለአባላት አቅም ግንባታ ሥልጠናዎች፣ የግልግል ዳኝነት እና ኤክስፖርትን ለማስፋፋት እንዲሁም የንግድ ነክ መረጃዎችን ያካተተውን አዲሱ የምክር ቤቱ የዲጂታል ሲስተም (Ethiopian Chamber Digital System) አስመልክቶ በ Africom Technologies & iDaptive Data Fusion System ባለሙያዎች ገለፃ ተድርጓል።

የኢትዮጵያ የንግድ እና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ተ/ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ሲያስተላልፉ በምክር ቤቱ ቀደም ሲል በነበረው አሰራር የንግድ ማሳለጫ ስራዎች (trade facilitation operations) በአብዛኛው ማንዋል የነበሩ በመሆኑ ነጋዴዎች በምክር ቤቱ በአካል ተገኝተው ፎርሞችን ለመግዛትና ለመሙላት ይገደዱ ነበር ብለዋል፡፡ አሁን በተዘጋጀው ዘመናዊ የዲጂታል አገልግሎት አሰጣጥ ግን የንግዱ ማህበረሰብ ከየትኛውም የዓለም ክፍል እና ቦታ ሆኖ አገልግሎቱን ማገኘትና መጠቀም እንደሚችሉ ተ/ዋና ፀሀፊው አክለው ተናግረዋል።

የዲጂታል አገልግሎቱን በይፋ ያስጀመሩት የኢፌዴሪ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ አቶ እንዳለው መኮንን እንደተናገሩት ምክር ቤቱ አገልግሎት አሰጣጡን ከማኑዋል ወደ ዲጂታል በማሸጋገር አባላቱ እና የንግዱ ማህበረሰብ በተመቻቸው ጊዜና ቦታ አገልግሎት ማግኘት የሚችችሉበትን አዲስ የዲጂታል ፕሮጀክት በማዘጋጀቱ ትግበራ መጀመሩ ትልቅ አድናቆት ይገበዋል፤ ሚኒስቴር መሰሪያ ቤቱም በሚፈለግበት ሁሉ እገዛ ያደርጋል።

በትሬድ ማርክ ኢስት አፍሪካ የኢትዮጵያ ዋና ዳይሬክተር አቶ አብነት በቀለ፤በበኩላቸው የንግዱን ምህዳር ምቹ ለማድረግ ትሬድ ማርክ ኢስት አፍሪካ በለጋሾች በኩል የኢትዮጵያን መንግስት ለመደገፍ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከሚያስተባብራቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ የምክር ቤቱ የዲጂታል አገልግሎት ፕሮጀክት አንዱ መሆኑን በመጥቀስ፤ ጊዜ እና የግብይት ወጪዎችን ቆጣቢ የሆነውን የዚህን ፕሮጀክት አጠቃቀም ለንግዱ ማህበረሰብ ሙሉ በሙሉ ለማስተዋወቅ ወደፊት ቀጣዩ ደረጃ ወሳኝ ነው ብለዋል።

የመዝጊያ ንግግር የደረጉት የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ኢ/ር መለአኩ እዘዘው በበኩላቸው አዲሱን የዲጂታል ሲስተም አተገባበር ምክር ቤቱ አቅሙን ገንብቶ በራሱ ሙሉ በሙሉ እስከ ሚያስተዳድረው ድረስ ሲፍትዌሩን ያዘጋጀው ድርጅት በቀጣይ ለሁለት አመት የቴክኒክ እገዛ እንደሚያደርግና በኤሌክትሮኒክ የአንድ መስኮት አገልግሎትን(Electronic Single Window Service) አስመልክቶ ከገቢዎች ሚኒስቴር ጋርም በመተባበር በመስራት የንግዱን ማህበረሰብ በበቃት እንደሚያገለግሉ ገለፀዋል፡፡ በመጨረሻም በእለቱ ትግበራውን በይፋ የጀመረው የምክር ቤቱ የዲጂታል ሲስተም እውን እንዲሆን በገንዘብና በቴክኒክ የረዱትን የአይርላንድ መንግስት፣ የትሬድ ማርክ ኢስት አፍሪካ እና Africom Technologies & iDaptive Data Fusion System ድርጅት አመስግነዋል፡፡

በዚህ የዲጂታል አገልግሎት ይፋ የማስጀመር ስነ-ስርዓት ላይ የኢፌዴሪ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር መሰሪያ ቤትን ጨምሮ ከፍተኛ የመንግስት ስራ ሀላፊዎች እና የንግዱ ማህበረሰብ ተወካዮች ተገኝተውበታል፡፡

◈

## ተ/ዋና ፀሀፊው የኒዉዝላንድ አምባሳደርን ተቀብለው አነጋገሩ

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ተ/ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የምክር ቤቱ የስራ ሀላፊዎች ጋር በመሆን መጋቢት 30 ቀን 2014 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የኒዉዝላንድ አምባሳደር ሚሰተር ሚካኤል አፐተንን በፅ/ቤታቸዉ ተቀብለዉ አነጋገሩ፡፡

ምክር ቤቱ በአዋጅ የተቋቋመ ሆኖ በስሩ የክልል ንገድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶችን ፣ የሁለት ከተማ የንገድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶችን እና አገር አቀፍ የዘrርፍ ማህበራት ምክር ቤቱን ጨምሮ የዘርፍ ማህበራትን በፈቃደኛ አባልነት በስሩ በማካተት የተመሰረተ የግሉ ዘርፍ ድምፅ ተቋም መሆኑን በመጥቀስ በዋነኝነት የአድቮኬሲና ምርምር፣ የአቅም ግንባታ አና የንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት ስራዎችን እንደሚሰራ አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ያሏትን ዘርፈ-ብዙ የንግድና ኢንቨስትመንት ሀብቶች ከገለፁ በኋላ ምክር ቤቱ ከኢምባሲው ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር የንግዱ ማህበረሰብ በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ እነዲሆን በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ንግድ እና ኢንቨስትመንት የበለጠ ማስፋፋት እንደሚፈልጉ አስምረውበታል፡፡ በመጨረሻም ምክር ቤቱ በግንቦት ወር 2014 ዓ.ም በሚያዘጋጀው 12ኛው የኢትዮ- ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ኢምባሲውና የኒውዝላንድ ኩባንያዎች እንዲሳተፉ ጋብዘዋል፡፡

አምባሳደር ሚሰተር ሚካኤል አፐተን በበኩላቸው የኒውዝላንድ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በቁጥር ጥቂት እንደሆኑና ሁለቱ አገሮች የንግድና ኢንቨስትመንት እድሎቻቸው ላይ የበለጠ በመስራት በመካከላቸው ያለውን የቢዝነስ ትስስር የበለጠ ማጎልበት እንደሚገባ ተናግረዋለ፡፡ እ.ኤ.አ. በ2019 377000 የኒውዝላንድ ዶላር የሚገመቱ እንደ ማሽኖች፣ ብረታብረትነና መሽነሪዎች የመሳሰሉ ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ በመላክ እንዲሁም



ከኢትዮጵያ ደግሞ ወደ 6.9 ሚሊዬን የኒውዝላንድ ዶላር የሚገመቱ እንደ ቡና የመሳሰሉ የእርሻ ምርቶችን ኒውዝላንድ ያስገባች መሆኗን በመጥቀስ የንግድ ሚዛኑ ወደ ኢትዮጵያ ያደላ ነው ብለዋል፡፡ አገራቸው በቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግር፣ በስልጠና እና የገንዘብ ድጋፍ የመሳሰሉትን ለኢትዮጵያ በማድረግ የሁለቱ አገሮች የንግድ ማህበረሰቦች በጋራ በሚጠቀሙበት አግባብ ወደፊት ከምክር ቤቱ ጋር በትብብር እንደሚሰሩ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

ሁለቱ ወገኖች በንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት፣ በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥና የእዉቀት ሽግግር፣ በገንዘብና ቴክኒክ ድጋፍ እና ሌሎችም በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ በቀጣይ በትብብር በሚሰሩበት አግባብ ላይ ተወያይተዋል ::

◈

# የኢትዮ-ቱርክ የንግድና የኢንቨስትመንት ፎረም በአንካራ ተካሄደ

በቱርክ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ኤምባሲ ከኢንዱስትሪ ባለቤቶች ኮንፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ያዘጋጀው የሀገራችንን የወጪ ንግድ እና የኢንቨስትመንት እድል የሚያስተዋውቅ ፎረም በቱርክ አንካራ ተካሄደ።

በፎረሙ በቱርክ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተሰማሩ ከ100 በላይ ባለሃብቶች እንዲሁም ከ25 በላይ የኢትዮጵያ የንግድ ማህበራት ምክር ቤት አባላት ተሳትፈዋል።

የቱርክ የኢንዱስትሪ ባለቤቶች ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ፈርዱን ሲቫሂሮግሉ በመክፈቻ ንግግራቸው፥ ኮንፌዴሬሽኑ ከ25 ሺህ በላይ ኩባንያዎች በአባልነት በማቀፍ በቱርክ የሚገኙ የሀገሪቱ ባለሃብቶችን ከተለያዩ ሀገራት ጋር በማገናኘት የኢንቨስትመንትና የንግድ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚሰራና መሆኑን ተናግረዋል።

በቱርክ መንግስት የሚደገፍ የሲቪክ ማህበር መሆኑን በመጠቆምም የዚህ አይነት ፎረም ከኤምባሲው ጋር በጋራ መዘጋጀቱ በሁለቱ ሀገራት መካከል ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነትን የበለጠ ለማሳደግ እንደሚረዳ ገልጸዋል ።

ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ የኮንፌዴሬሽኑ በአዲስ አበባ ቢሮ እንደሚከፍት አስታውቀዋል።

በቱርክ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር አደም መሀመድ በበኩላቸው፥ በኢትዮጵያ እና በቱርክ መካከል ያለውን መልካም ግንኙነት በማንሳት፥ በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የተደረገው ጉብኝት የዚህ መልካም ግንኙነት እድገት አይነተኛ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሁለቱ ሀገራት መሪዎች በኢንቨስትመንት፣ በንግድና በፖለቲካው ዘርፍ በጋራ ለመስራት መስማማታቸውን በመግለጽ ስምምነቶቹን ወደ ተግባር ለመቀየር በትብብር መስራት እንደሚገባ ነው የጠቆሙት።

በተጨማሪም የኢትዮጵያን የንግድ እና የኢንቨስትመንት ምቹ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ለቱርክ ባለሃብቶች ጥሪ አቅርበዋል።

የሀገራችንን የገቢና ወጪ ምርቶች አስመልክቶ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ቦርድ አባል ዶ/ር አይናለም አባይነህ ንግግር ያደረጉ ሲሆን፥ የወጪ ምርቶችን ወደ ቱርክ ገበያ ለማስገባት ለሚፈልጉ የቱርክ ባለሀብቶች ሁሉ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ እና በሁለቱ ሀገሮች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት የበለጠ ለማሻሻል እንደሚሰሩ ገልጸዋል።

በፎረሙ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ተ/ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ፥ በኢትዮጵያ በኩል ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮች ማቅረባቸውን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/121554-2/

# ምግብ የሚያቀነባብሩ 28 ፋብሪካዎች በመገንባት ላይ መሆናቸው ተነገረ

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ 28 የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በግንባታ ላይ መሆናቸውን፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በምግብ ማቀነባበር ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልጉ ኩባንያዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለመሥራት ፍላጎት እያደገ መሆኑንና ከ110 በላይ ድርጅቶች ዘርፉን ለመቀላቀል በሒደት ላይ መሆናቸውን፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ዳይሬክተር አቶ አያልነህ አባዋ ለሪፖርተር ገልጸዋል።

ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው በምግብ ማቀነባበር ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት ካሳዩ ድርጅቶች መካከል፣ 28 ያህሉ የፋብሪካ ግንባታ መጀመራቸውን አስረድተዋል፡፡ ፋብሪካዎቹ በ2014 በጀት ዓመት ውስጥ ፈቃድ ያገኙ መሆናቸውን፣ ግሉኮስና የተለያዩ ምግቦች በማቀነባበር ሥራ ላይ እንደሚሰማሩ ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በምግብ ማቀነባበሪያ ዘርፍ ሰባት ፋብሪካዎች ብቻ መኖራቸውን ገልጸው፣ በተለይም በአቮካዶ ዘይት ምርት ላይ እየሠሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ስምንት ወራት ውስጥም ድርጅቶቹ ከ300 ሺሕ ሊትር በላይ የአቮካዶ ዘይት ለሆላንድ ገበያ በማቅረብ፣ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘታቸውን አቶ አያልነህ ጠቁመዋል፡፡ የሚገነቡት የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በተለይም በሐዋሳ፣ በይርጋለምና በቡሬ አግሮ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ እንደሚገኙ፣ በማምረት ላይ የሚገኙት ደግሞ በይርጋለም አግሮ ኢንዱስትሪ ውስጥ መሆናቸው ተገልጿል።

አግሮ ኢንዱስትሪዎችን ከአርሶ አደሮች ጋር በማስተሳሰር የግብዓት አቅርቦት ችግር እንዳይኖር በማድረግ፣ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል። እስካሁንም ከ135 ሺሕ በላይ አርሶ አደሮች ከፓርኮቹ ጋር ተሳስረው አቮካዶን ጨምሮ ሌሎችም ምርቶችም ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

በመቋቋም ላይ ከሚገኙት ፋብሪካዎች በተጨማሪ 82 ድርጅቶች ከመንግሥት ጋር ንግግር በማድረግ ላይ መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ አያልነህ፣ አስፈላጊውን መሥፈርት የሚያሟሉት ድርጅቶች ወደ ፋብሪካ ግንባታ እንደሚገቡ ገልጸዋል። በመገንባት ላይ ካሉትና በንግግር ላይ ከሚገኙት ፋብሪካዎች ውስጥ 80 በመቶ የሚሆኑት የአገር ውስጥ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/25017

# የአገር ውስጥና የተለያዩ አገሮች ድርጅቶች የሚሳተፉበት የፈርኒቸር ዓውደ ርዕይ እየተካሄደ ነው



የአገር ውስጥና ከተለያዩ አገር የተውጣጡ የፈርኒቸር አምራቾችና አቅራቢዎች የንግድ ትስስር የሚፈጥሩበት እንዲሁም የልምድ ልውውጥ የሚወስዱበት ዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕይ እየተካሄደ ነው፡፡

ፕራና ኤቨንትስና አፍሪካን ትሬድ ፎር ፓርትነርስ በጋራ በሚያዘጋጁት ዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕይና ኮንፈረንስ ከ60 በላይ ኩባንያዎች የሚሳተፉ ሲሆን፣ በዓውደ ርዕዩም ኢትዮጵያን ቴክኖሎጂዎችንና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም የእንጨት ምርቶችን ለዓለም እንድታስተዋውቅ ይረዳታል ተብሏል፡፡

ከመጋቢት 29 እስከ ሚያዝያ 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ «ንግድዎን በመቅረዝ ላይ ያኑሩ» በሚል መሪ ቃል ለሦስተኛ ጊዜ በስካይላይት ሆቴል በሚካሄደው ዓለም አቀፍ ዓውደ ርዕይና ኮንፈረንስ ከ4,000 በላይ የንግዱ ተዋናይ አባላትና ጎብኚዎች ይስተናገዱበታል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

የአፍሪካ ትሬድ ፎር ፓርትነርስ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ አክሊሉ በለጠ እንደገለጹት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የፈርኒቸር ሥራ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው፣ ይህንንም ታሳቢ በማድረግ የማኑፋክቸሪን ምርቶችን በማሳደግ በኢትዮጵያ የሚገኙ የዘርፉ ተዋናዮችን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያ ለእንጨት ሥራ የሚሆኑ ግብዓቶች የሞላባት አገር እንደመሆኗ፣ ያላትን ሀብት በመጠቀም ዓለም የደረሰበትን የሥልጣኔ ጥግ በማድረስ፣ ከውጭ አገር የሚገቡ የእንጨት ሥራዎችን ለማስቀረትና በአገር ውስጥ ጥራት ባለው መልኩ በማምረት የገበያ ሰንሰለቷን ማሳደግ እንደሚኖርባት አክለው ገልጸዋል፡፡

በዘርፉ ላይ የተሰማሩ አብዛኛው ኢንተርፕራይዞች ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንደሚያቀርቡ፣ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ መንግሥት በጉዳዩ ምን እየሠራ ነው? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ የፓናል ውይይት የሚካሄድ መሆኑን አቶ አክሊሉ አስረድተዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚስተዋለው መጠነ ሰፊ የመሠረተ ልማት ልዩ ልዩ ግንባታዎች፣ ማኅበረሰባችን ወደ ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ በፍጥነት ከመግባት ጋር ተያይዞ የገበያው ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ በማደጉ ለፈርኒቸር፣ ለቤተ ውበትና ግንባታ አጨራረስ ዘርፎች የፈጠራ ሥራ መጨመርና ዕድገት መንገድ መከፈቱን አብራርተዋል፡፡

በዚህም መሠረት በዓውደ ርዕዩ ላይ የአገር ውስጥ አምራቾችንና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን በአንድ ጣሪያ ሥር በማሰባሰብ ከመላ ኢትዮጵያ ከሚመጡ ከመንግሥት፣ ከንግዱ ማኅበረሰብ፣ ከዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብና ከበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በመገንባት ላይ ከሚገኙ ባንኮች፣ ሆስፒታሎች፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንግድ ማዕከላት፣ ሲኒማ ቤቶች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ከአነስተኛና ጥቃቅን በማደግ ላይ ለሚገኙ የፈርኒቸር አምራቾች እንዲሁም ወኪል ሆነው በክልል ከተሞች ለመሥራት ለሚፈልጉ ሁሉ በፈርኒቸር፣ በቤተ ውበትና በግንባታ አጨራረስ ምርትና አገልግሎቶች ላይ የሚተጉ ግዙፍ የአገር ውስጥ አምራቾችና የውጭ አገር አቅራቢዎች ጋር የገበያ ትስስር ለመፍጠር ያለመ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዓምና በተካሄው ዓውደ ርዕይ ላይ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የንግድ ዘርፉ ተዋናዮች መሳተፋቸውን፣ አብዛኞቹም የንግድ አቅጣጫቸውን የማሳደግ አቅም እንዳገኙ ተናግረዋል፡፡

ከውጭ አገር የሚመጡ ምርቶችን አገር ውስጥ በማምረት ለተለያዩ ተቋማት አገልግሎት በመስጠትና ተደራሽ በማድረግ እየሠሩ መሆኑን የሚናገሩት የአይዞ ማኑፋክቸሪነግ ማኔጂንግ ዳይሬክተር አቶ ፋሲል ክፍለኢየሱስ ናቸው፡፡

ለሦስት ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ በዓመት 11 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ የፈርኒቸር ግብዓቶችን ወደ ተለያዩ አገሮች ልካለች ያሉት ዳይሬክተሩ፣ በዚህም የተሰማሩ ተዋናዮች ትኩረት በመስጠት የአገር ውስጥ ምርት ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በተለያዩ አገሮች የሚገኙ የዘርፉ ተዋናዮች ለፈርኒቸር ምርት ትኩረት እንደሚሰጡ፣ ኢትዮጵያም በዚህ ተጠቃሚ እንድትሆን መንግሥት መዋዕለ ንዋዩን ማፍሰስ እንደሚኖርበት ገልጸዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት እ.ኤ.አ. በ2016 ያወጣው ጥናት እንደሚጠቁመው፣ ኢትዮጵያ የፈርኒቸር ምርቶችን ከውጭ አገር በማስገባት ከደቡብ አፍሪካ፣ ከናይጀሪያ፣ ከአንጎላና ከሴኔጋል በመቀጠል ከአፍሪካ በአምስተኛ ደረጃ ትቀመጣለች፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ከኬንያ በመቀጠል ሁለተኛዋ ግዙፍ የገበያ መዳረሻም ናት፡፡

በኢትዮጵያ በፈርኒቸር ለቤት ውበትና ለግንባታ አጨራረስ ኢንዱስትሪ ዘርፉ ተገቢውን ዕውቅና ለመስጠትና ለመደገፍ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ የአገር ውስጥንና የውጭ ባለሀብቶችን ለማበረታታት የገበያ ትስስርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለመፍጠር ዓውደ ርዕዩ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው ጠቁመዋል፡፡

በቀጣናው በምጣኔ ሀብትና በኢንዱስትሪ ዘርፉ ላይ ያሉትን ሚና በዘላቂነት እንዲሁም በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስቀጠል፣ በተለይም ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ለማረጋገጥ ዓውደ ርዕዩ አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት ከታች ጀምሮ የሚገኙ የዘርፉ ተዋናዮችን በመደገፍና የአቅም ግንባታ በማድረግ የፈርኒቸር አምራቾችን ማሳደግ እንደሚኖርበት ጠቁመዋል፡፡

ባደጉ አገሮች አብዛኛው የቤት ውስጥ ዕቃዎች በእንጨት ሥራ የተሠሩ መሆናቸውን፣ ይህም ምን ያህል ለዘርፉ ትኩረት እንደተሰጠው ማሳያ ነው ብለዋል፡፡

በዓውደ ርዕዩም በፖሊሲ አውጪዎችና በንግዱ ማኅበረሰብ ባለሙያዎች መካከል በዘላቂ ልማት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ የተመረጡ ርዕሶች ላይ ዓውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡

ዓውደ ጥናቱ ሙያዊ ደረጃቸውንና ሥነ ምግባርን የሚሸፍን ከመሆኑ ባሻገር፣ ኢትዮጵያ በዘርፉ ለምታካሂደው የምጣኔ ሀብት ልማት የአቅም ግንባታ ለመፍጠር የሚያስችል ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎንም ዓለም አቀፍ የንግድ አቀማመጥና የዳሰሳ ጥናት ዘዴዎችን በሚያሳይ መልኩ በዘርፉ የበርካታ ዓመታት ልምድ ባላቸው የአገር ውስጥ እንዲሁም ከእንግሊዝ፣ ከፖላንድ፣ ከቱርክና ከኬንያ በሚመጡ ባለሙያዎች ጥናት ይቀርባል፡፡

የአፍሪካ ፍላጎት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ እ.ኤ.አ. በ2018 በአጠቃላይ ወደ አፍሪካ የገቡ የፈርኒቸር ምርቶች መጠን ወደ አምስት ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ እንደነበር በወቅቱ ተገልጿል፡፡

ከከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞም እ.ኤ.አ. በ2030 አሁን ባለው የዕድገት መጠን ከቀጠለ ከ500 ሚሊዮን በላይ የአፍሪካውያን ወደ ተለያዩ አገር ከተሞች ይንቀሳቀሳሉ ተብሏል፡፡

ይህም በአፍሪካ ውስጥ ከተሞች ያሉ የሪል ስቴት መኖሪያ፣ የቢሮ ቦታ፣ ሆስፒታሎች፣ ሆቴሎችና ትምህርት ቤቶች ጥልቅ ፍላጎትን ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ በምሥራቅ አፍሪካ በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ውስጥ የፈርኒቸር፣ የቤት ውበትና የግንባታ አጨራረስ ኢንዱስትሪ ምርቶች የገበያ ፍላጎት ከዕጥፍ በላይ እየጨመረ ይመጣል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25133

# የግብር ከፋይ ቅሬታዎችን ይፈታል የተባለ መመርያ ተዘጋጀ

የገቢዎች ሚኒስቴር የሒሳብ መዝገብ አያያዝ መመርያ ቁጥር 152/2011 በማሻሻል፣ በብድር አሰጣጥና በካፒታል ማሳደግ ምዝገባ ሒደት ላይ እየተፈጠሩ ያሉ ቅሬታዎችን ለመፍታት ያስችላል የተባለ ረቂቅ ማዘጋጀቱን አስታወቀ።

ከአራት ዓመታት በፊት የወጣው የሒሳብ አያያዝ መመርያ በሥራ ላይ ከዋለ ጊዜ ጀምሮ በወቅቱ ከውልና ማስረጃ፣ እንዲሁም ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ያለው አሠራር የተቃረነ እንደሆነ በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ኦዲት ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ አበበ ገልጸዋል።

አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው መመርያ ከታክስ አስተዳደር ሥርዓት ጋር የሚጣረስና ወቅቱ ከሚፈልገው የቢዝነስ ተለዋዋጭነት ጋር የሚጋጭ መሆኑን በመጥቀስ፣ በተለይ በብድርና በካፒታል ማሳደግ ምዝገባ ሒደት ላይ ችግሮች ማጋጠማቸውን ተናግረዋል።

አዲሱ መመርያ ከፋይናንስ ተቋማት ብድር በሚወሰድበት ወቅት ገንዘቡ በቀጥታ ለተጠየቀበት ሥራ መዋሉ መረጋገጥ እንዳለበት ያዛል። በተጨማሪም ከፋይናንስ ተቋማት ውጪ በመንደር ውል የሚወሰዱ ብድሮች በግብር ሰብሳቢው አካል ዕውቅና ያገኛሉ ተብሏል።

መመርያው በ2011 ዓ.ም. ከመውጣቱ በፊት የነበሩ የሒሳብ መዝገቦችን ኦዲት ማድረግ ቅሬታ ሲፈጥር የነበረ ሲሆን፣ በአዲሱ መመርያ መሠረት ግን ቀደም ሲል የነበሩ የሒሳብ ሰነዶች አይመለከታቸውም፡፡

ስለሰነድ አቀራረብና ሰነድ ተሟልቶ ባልቀረበ ጊዜ ሊኖር ስለሚገባው አሠራር፣ እንዲሁም ከውልና ማስረጃና ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በተያያዘ የካፒታል ማሳደግ ምዝገባ ለማድረግ የሚሰጠው ጊዜ በቂ ሳይሆን ሲቀር፣ በግብር ከፋዮች ላይ ጫና የሚያሳድሩ ሆነው መገኘታቸውን አቶ ብርሃኑ ገልጸዋል።

በዚህም መሠረት በካፒታልነት እንዲመዘገብ ጥያቄ ቀርቦበት ያልተመዘገበ ሒሳብ፣ በገቢነት ተመዝግቦ ግብር እንዲከፈልበት የሚደረግ በመሆኑ፣ ይህም ግብር ከፋዮችን የሚጎዳ መሆኑን አብራርተዋል።

አዲሱ መመርያ በተለይም የአክሲዮን ማኅበራት ጠቅላላ ጉባዔያቸውን አድርገው ካፒታል እንዲያድግ ከወሰኑበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ውስጥ፣ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና በውልና ማስረጃ እንዲያስመዘግቡ የሚያዝ ሲሆን፣ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካልተጠናቀቀ ተጨማሪ ጊዜ ታሳቢ እንዲደረግ የሚጠይቅ ነው።

አዲሱ መመርያ ከውልና ማስረጃ፣ እንዲሁም ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ንግግር እየተደረገበት እንደሚያገኝ የገለጹት አቶ ብርሃኑ፣ ከአንድ ወር በኋላ ፀድቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/24923

## የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመር ለኮንትራክተሮች ትልቅ ፈተና መሆኑ ተገለጸ

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን፣ በግንባታ ዕቃዎች ላይ የታየው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ፣ በኮንትራት በተቀበላቸው ፕሮጀክቶች ከመፈተኑም በተጨማሪ፣ በቀጣይ ለሚረከባቸው ፕሮጀክቶችም ምን ማድረግ እንዳለበት እንዳሳሰበው አስታወቀ፡፡

የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ ከሁለት እስከ ሦስት እጥፍ መጨመራቸው ለኮንትራክተሮች ትልቅ ፈተና በመሆኑ፣ ከዚህ በኋላ ወደ ኮርፖሬሽኑ የሚመጡ ኮንትራቶች ላይ ትኩረት አድርጎ እይሠራ ነው ሲሉ በኮርፖሬሽኑ የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች መምርያ ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥንፉ ሙጩ ተናግረዋል፡፡

ለጊዜው ቁጥራቸው በውል ያልታወቁ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎች በግብዓት እጥረትና ዋጋ መወደድ ምክንያት ከገበያ ውጪ መሆናቸው እየተነገረ ነው፡፡

ኮርፖሬሽኑ የገበያ ዋጋ የማይረጋጋ ከሆነ ችግር ውስጥ የሚገባ መሆኑን ገልጾ፣ ከዚህ በኋላ የሚመጡ ኮንትራቶችን አሁን ባለው ዋጋ መቀበል እንደማይችል አስታውቋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በተያዘው በጀት ዓመት 37.1 ቢሊዮን ብር የሚያወጡ 49 ፕሮጀክቶችን ቀደም ሲል ባስገባቸው ግብዓቶችና በአገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶችን በመጠቀም ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ አቶ ጥንፉ ገልጸዋል፡፡

በአገር ውስጥ የሚተኩ ምርቶችን አሁን ካለው የምርት መጠን  በላይ ጨምሮ ለማምረት እየሠራ መሆኑንም ኮርፖሬሽኑ አስታውቋል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲቪል ኢንጂነሪንግ ትምህርት ክፍል ኃላፊ አበበ ድንቁ (ፕሮፌሰር) በበኩላቸው፣ የግንባታ ግብዓቶችን ከዚህ ቀደም በአገር ውስጥ መተካት ጥረት ባለመደረጉ አሁን ሁኔታዎችን እያከበዳቸው ነው ብለዋል፡፡

«በአሁኑ ጊዜ አገሪቱ ያለችበት የፀጥታ ችግር በቅፅበት በአገር ውስጥ አምርተን ፍላጎት ማሟላት አንችልም፡፡ በየክልሉ ያሉ እንደ ዕምነበረድ ያሉ ምርቶችን ለመጠቀም የሰላም አለመኖር ትልቅ ችግር እየፈጠረ ይገኛል፤» ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በአገር ውስጥ የሚመረት የዕምነበረድ ውጤት ዋጋ ከዓመት በፊት ከነበረው መቶ ፐርሰንት የነበረ መሆኑን፣ ከወር በፊት ከነበረው ደግሞ 20 በመቶ መጨመሩን አበበ (ፕሮፌሰር) አክለዋል፡፡

ግንባታ የረዥም ጊዜ ሥራ ስለሆነ ሲጀመር ትክክለኛ የዋጋ ተመን ሊኖር ስለማይችል 20 በመቶ ጭማሪ ወይም ቅናሽ ሊኖረው እንደሚችል፣ ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የመቀነስ ሁኔታ ባይታይም በተገመተበት ዋጋ ስለማይጠናቀቅ የዋጋ ጭማሪ መከተሉ አይቀሬ ነው ብለዋል፡፡

የግንባታ ግብዓቶች ዋጋ የሚጨምርባቸው ምክንያቶች ከውጭ የሚመጡ ዕቃዎች የሚገቡበት የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የነዳጅ ዋጋ መጨመር፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ታሪፍ መጨመርና ሰው ሠራሽ የዋጋ ጭማሪ መሆናቸውን ደግሞ የኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ግርማ ሀብተማርያም አስረድተዋል፡፡

በተቆረጠ ዋጋ የሚዋዋሉ ኮንትራክተሮች በአሁኑ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ከገበያ የመውጣት ዕድላቸው ሰፊ ነው ሲሉ አበበ (ፕሮፌሰር) ጠቁመው፣ እነዚህ ኮንትራክተሮች ሠርተው ከሚከስሩ ይልቅ ፕሮጀክቶቹን ማቆማቸው የተሻለ ነው ብለዋል፡፡

ባልተቆረጠ ዋጋ የሚሠሩ ፕሮጀክቶች የዋጋ ማሻሻያ ማድረግ የሚችሉት 20 በመቶ ቢሆንም፣ አሁን ባለው የገበያ ዋጋ መሠረት ግን እስከ 50 በመቶ ጭማሪ በማድረግ ከሕግ ውጪ መሄድ ይኖርባቸዋል ሲሉም አክለዋል፡፡

«ይህ ሕግ ከመጣሱ በፊት የሚመለከተው አካል ደንቡን ማሻሻል ይኖርበታል፣ ይህ ደንብ የማይሻሻል ከሆነ ደግሞ የግል ብቻም ሳይሆን የመንግሥት ፕሮጀክቶችም ሙሉ ለሙሉ ይቆማሉ፤» ብለዋል፡፡

ወደፊት የሚከናወኑ የመንግሥት ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ አሁን ከሚጠቀሙበት የግንባታ በጀት በእጥፍ እንዲያድግላቸው ለፓርላማ ጥያቄ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል በማለት አበበ (ፕሮፌሰር) አስረድተዋል፡፡

በርካታ የዩኒቨርሲቲዎች፣ የመንገድና ሌሎች ትልልቅ የመንግሥት ፕሮጀክቶች በአሁኑ ጊዜ መቆማቸውን ገልጸው፣ ምክንያቱ ደግሞ ለአንድ መሥሪያ ቤት የሚፀድቀው ዓመታዊ የግንባታ በጀት አሁን ካለው  የዋጋ ጭማሪ ጋር ባለመመጣጠኑ ነው ብለዋል፡፡

ኮንስትራክሽን በዕድገት ላይ ላሉ አገሮች ትልቁ የሥራ ዕድል የሚፈጠርበት ዘርፍ ስለሆነ አስቸኳይ መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባ የጠቆሙት አበበ (ፕሮፌሰር)፣ ይህ ዘርፍ ከተናጋ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ችግር ውስጥ ይከተዋል ብለዋል፡፡

የመንግሥት ጨረታዎችን አለማግኘት፣ ብሔራዊ ባንክ ለተወሰነ ጊዜ የብድር ዕገዳ ማድረጉ፣ በፀጥታ ችግር ሳቢያ፣ በኮቪድ-19 እና በርካታ ፕሮጀክቶችን በሞኖፖል መያዝ፣ ለኮንትራክተሮች ከገበያ መውጣት ምክንያቶች ናቸው ሲሉ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ ግርማ ጠቁመዋል፡፡

ከ30 ዓመታት በፊት የተመሠረተው የሥራ ተቋራጮች ማኅበር ከ2,400 በላይ አባላትን በመያዝ ለዘርፉ ማነቆ የሆኑ መመርያዎች እንዲሻሻሉ የተለያዩ ሥራዎችን እንደሚያከናውን ይነገራል፡፡

አብዛኞቹ የግንባታ ዕቃዎች ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸውና የተለያዩ የዋጋ ዓይነቶች መኖራቸው፣ ለኮንትራክተሮች ትልቅ ችግር መፍጠራቸውን፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ባህሪም በጣም ተለዋዋጭ መሆኑን ያወሱት አቶ ግርማ፣ መንግሥት በግንባታ ግብዓቶች ላይ የገበያ ቁጥጥር ማድረግ አለበት ብለዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25144

## መንግሥት እጁን የታሰረበት የአገር ውስጥ የነዳጅ ምርት ገበያ

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ከውጭ ከምታስገባቸው ምርቶች መካከል ነዳጅ በመጠንም ሆነ በወጪ በግንባር ቀደምነት ይቀመጣል፡፡ የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም ለሪፖርተር እንደገለጹት፣ የኢትዮጵያ ዓመታዊ የነዳጅ ፍጆታ በአሁኑ ወቅት 3.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 65 በመቶ ቤንዚን እንደሆነ የገለጹት አቶ ታደሰ፣ አገሪቱ ለነዳጅ ግዥ የምታወጣው ዓመታዊ ወጪም በየዓመቱ እያደገ መሆኑንም ያመለክታሉ፡፡ ዋና ሥራ አስኪያጁ እንደገለጹት፣ በአሁኑ ወቅት ለነዳጅ ግዥ በየወሩ 250 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ይደረጋል፡፡

በወር ይህን ያህል ወጪ የሚወጣበት የነዳጅ ምርት ግን በየጊዜው የአገር ውስጥ ገበያ የችግር ምንጭ ሆኖ ይስተዋላል፡፡ ነዳጅ ጠፋ ተብሎ የሚፈጠረው ትርምስ እንቅስቃሴዎችን ሲያስተጓጉል፣ ተጠቃሚዎችን ሲያማርርና አጠቃላይ የንግድ ሥርዓቱን ሲያምስ ይታያል፡፡ ከሰሞኑንም ይኼው ከነዳጅ ጋር የተያያዘ የገበያ ቀውስና መስተጓጎል ተከሰቶ መነጋገሪያ ሆኗል። ችግሩ ከምን መነጨ ለሚለው ጥያቄ ባለድርሻ ከሚባሉ አካላት የተለያየ አስተያየት ሲሰጥበት ሰንብቷል፡፡ የአገር ውስጥ የነዳጅ ገበያ ችግር ከሰሞኑ የተከሰተ ብቻ አይደለም። ችግሩ ለዓመታት የዘለቀና በየጊዜው ደጋግሞ የሚከሰት መፍትሔ ያጣ በሽታ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ዘርፉ ሥርዓት ዓልባና በውስብስብ ችግሮች የተተበተበ፣ በተለይም ሌብነትና ደካማ ቁጥጥር የሚታይበት እንደሆነ ይነገራል፡፡

መንግሥት በከፍተኛ ድጎማ አድርጎ ለተጠቃሚዎች የሚያቀርበውና አገሪቱ ካላት ውስን የውጭ ምንዛሪ አብዛኛውን የምታፈስበት የነዳጅ ምርት ሥርጭትና ንግድ በአግባቡ የማይመራ ከመሆኑ ባሻገር፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ በሕገወጥ የነዳጅ ግብይት ውስጥ እጃቸውን አስርገው የሚዘውሩት መሆኑ ችግሩን ውስብስብና ለመፍትሔ አዳጋች እንዳደረገው ይጠቀሳል። አሁን ባለው ዓለም አቀፋዊ ቀውስ ደግሞ የነዳጅ ምርት ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ እየናረ መሆኑ ውስን የውጭ ምንዛሪ ክምችት ባላቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ የነዳጅ ምርት በዝቅተኛ ዋጋ የሚሸጥባት አገር ሆና ሳለ፣ የአገር ውስጥ የግብይት ሥርዓቱ የተዝረከረከ መሆን ለእንግልትና ለአጠቃላይ የገበያ ቀውስ ምክንያት በመሆኑ መንግሥት የአገር ውስጥ የነዳጅ ግብይት ሥርዓቱን መፈተሽ እንዳለበት የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ። በተደጋጋሚ ከሚከሰተው የነዳጅ እጥረት ጋር በተያያዘ አሉ የተባሉ አጠቃላይ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ዙሪያ የተጠናከረው ዘገባ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰሞኑን ነዳጅ ለምን ጠፋ?

ሰሞኑን በአዲስ አበባና በክልሎች የተከሰተው የነዳጅ እጥረት በርካታ ምክንያቶች አሉት፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አመራሮች ከሚያነሷቸው ችግሮች አንዱ የነዳጅ ምርቱን ከጂቡቲ ወደ መሀል አገር የሚያጓጉዙ ተሽከርካሪዎች በቀደመው ፍጥነት እንዳይደርሱ የመንገድ ብልሽት እክል ፈጥሮባቸዋል የሚለው ይገኝበታል፡፡ ለዚህም ከጂቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር የሚያወስደው መንገድ በከፍተኛ ደረጃ የተበላሸ መሆኑን ይጠቅሳሉ። በመሆኑም ከጂቡቲ - አዲስ አበባ ለመድረስ ሁለት ቀናት ይፈጅ የነበረው ጉዞ፣ በአሁኑ ወቅት አራትና አምስት ቀናትን እንደሚፈጅ በመጥቀስ ችግሩን ያመላክታሉ።

የዓለም ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ከዚህ በኋላ መንግሥት በምንም ሁኔታ ይህንን ጭማሪ መሸከም አይችልም ከሚል እሳቤም የተፈጠረው ውጥረትና ሥጋት መጨናነቁን እንደፈጠረም በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

በዓለም ሁለተኛዋ ነዳጅ አቅራቢ የሆነችው ሩሲያ በቀን ታቀርብ የነበረውን እስከ አሥር ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ከዓለም ገበያ መውጣቱ በራሱ ትልቅ ችግር እንደሆነ የሚገልጹት የኢትዮጵያ የነዳጅ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም፣ ይህ ችግር በተዘዋዋሪ በመላው ዓለም የነዳጅ ገበያ ላይ ተፅዕኖ እንደሚፈጥር ያመለክታሉ፡፡

ሰሞኑን በኢትዮጵያ የተፈጠረውን የነዳጅ አቅርቦት ችግር በተመለከተ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ውይይት ማድረጋቸውን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ከዚህ በኋላ ሁሉም ባለድርሻዎች በደንብ ክትትል እንዲያደርጉና የሚመለከተው ሁሉ በኃላፊነት እንዲሠራ መግባባት ላይ በመደረሱ ችግሩ አሁን ተቀርፏል ብለዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት እስከ ዓርብ ይህ ችግር ሙሉ በሙሉ መቀረፍ እንደሚገባው ውሳኔ ተላልፎ የነበረ ቢሆንም፣ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከዓርብ በፊት ችግሩ ሊቃለል ችሏል የሚል እምነትም አላቸው፡፡ መረጋጋቱ የተፈጠረው እጥረቱን ከመጠባበቂያ ዲፖ ማቅረብ በመቻሉ መሆኑን የሚጠቁሙ ወገኖች ደግሞ የነዳጅ እጥረት እንዳይፈጠር አሁንም መሠራት ያለበት እጅግ የበዙ ሥራዎች እንዳሉ ያመለክታሉ፡፡

በኢትዮጵያ ከነዳጅ አስተዳደርና አቅርቦት ጋር በተያያዘ በኢንዱስትሪው ከ25 ዓመታት በላይ ልምድ ያላቸው ሠርካለም ገብረ ክርስቶስ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከነዳጅ ሥርጭትና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር የሚታዩ ችግሮች የቆዩ መሆናቸውንና አሁን ተባብሰው መታየታቸውን ያመለክታሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ አንዱና ዋናው ጉዳይ የሕግ ማስከበር ችግር ነው፡፡ በኢትዮጵያ የነዳጅ ሥርጭት ታሪክ ውስጥ ከተወሰኑ ሌትሮች በላይ በዕቃ መግዛት እንደማይቻል ለዓብነት ያነሱት ባለሙያው፣ ይህ ክልከላ ምን ያህል ተፈጻሚ ይሆናል የሚለው ግን በጣም አጠያያቂ እንደሆነ ይገልጻሉ። ምክንያቱም ከማደያዎች በበርሜል በሌሊት ተቀድቶ እንደሚወጣ ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው፣ ከማደያ ጀርባ እዚያው ሲሸጥም በግልጽ ይታያል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከውጭ የመጣ ነዳጅ፣ ነዳጅ ማደያ ሳይደርስ ሌላ ቦታ ሁሉ ይራገፋል፡፡ በኮንትሮባንድ የሚመጣውንም መቆጣጠር አልተቻለም፡፡ ስለዚህ እጥረቱን እንዲህ ያሉ ተግራባት ሁሉ ይፈጥሩታል፡፡

በዚህ ዘርፍ ውስጥ ከፍተኛ ሙስና የሚስተዋል ስለመሆኑ የገለጹት ሠርካለም (ዶ/ር)፣ በተለይ በአሁኑ ወቅት በኮንትሮባንድ መልክ የሚወጣው ነዳጅ ጉዳይ መፍትሔ ያልተገኘለት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በኮንትሮባንድ የሚወጣውን ነዳጅ የሚቀበሉ አገሮች በኢትዮጵያ ከሚሸጥበት ዋጋ ሁለትና ሦስት እጥፍ በላይ ነዳጅ የሚሸጥባቸው በመሆኑ፣ ከኢትዮጵያ በኮንትሮባንድ የሚወጣውን ነዳጅ አገር ውስጥ ከሚሸጥበት ዋጋ በከፍተኛ ልዩነት እየተረከቡ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ እንዲህ ያለው ሕገወጥ ድርጊት ውስጥ ደግሞ የመንግሥት ባለሥልጣናት ጭምር እንዳሉበት ሠርካለም (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡ የነዳጅ ኩባንያ ኃላፊዎች፣ የትራንስፖርት ድርጅቶችና ማደያዎች ሳይቀሩ በዚህ ሕገወጥ ተግባር የሚመሳጠሩ በመሆኑ ለችግሩ መባባስ ምክንያት እንደሆነ ይጠቁማሉ።

እነዚህን ሰዎች መንግሥት ጭምር የሚያውቃቸው ቢሆንም፣ በሕግ ተጠያቂ አለማድረጉ ሕገወጥ ተግባሩ አሁንም እንዲቀጥል አድርጎታል ብለዋል፡፡ የኢትዮጵያ ነዳጅ አመላላሾች ማኅበርም በሰሞኑ ስብሰባው ይህንኑ የነዳጅ ኮንትሮባንድ ንግድ መኖር አረጋግጧል። ከባለድርሻ አካላት ገለጻ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየተገዛ የሚጓጓዘው ነዳጅ ከባለሀብቱ አቅምና ዕውቅና ውጪ በጥቅም በተሳሰሩ ተዋንያኖች በቅንጅት ወደ ጎረቤት አገሮች በኮንትሮባንድ መልክ እየወጣ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገሩን አሳዛኝ የሚያደርገው በመንግሥት ጭምር እየታወቀ ሕጋዊ ዕርምጃ ያለመወሰዱ ሲሆን፣ ይህም የኢትዮጵያን የነዳጅ ዘርፍ ችግር መፍትሔ አልባ አድርጎታል።

በዚህ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ የነዳጅ አመላላሽ ባለንብረቶች ማኅበር ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ፀጋ አስማረ፣ ይህንን ሕገወጥ ድርጊት ለመከላከል ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የትራንስፖርት ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ የምክክር መድረክ ችግሩን ለመቅረፍ የመፍትሔ አቅጣጫ የተቀመጠ ቢሆንም፣ ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር የቁጥጥር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ለዘርፉ ትልቅ ፈተና እንደሆነ ሰሞኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚታየው የነዳጅ እጥረት ሌላው መንስዔ የነዳጅ ኩባንያዎችን የሚተዳደሩበት አዋጅ ላይ ያለው ክፍተት እንደሆነ ሠርካለም (ዶ/ር) ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ 40 የሚሆኑ የነዳጅ አዳይ ኩባንያዎች መኖራቸውን የሚጠቅሱት ባለሙያው፣ እነዚህ ኩባንያዎች የተቋቋሙበት ይህ አዋጅ አንድ የነዳጅ አዳይ ኩባንያን ለማቋቋም የሚጠይቃቸው መሥፈርቶች በዘርፉ ለሚታዩ ችግሮች ሌላው ምክንያት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ በአዋጁ ድንጋጌ መሠረት አንድ ኩባንያን ለማቋቋም የሚጠይቀው መሥፈርት ሦስት ነዳጅ ማደያዎችና አንድ ነዳጅ ማከማቻን ማሟላት ብቻ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ አዋጁ በዚህ ዘርፍ ለመሰማራት የማያስቀምጠው ዝቅተኛ የኢንቨስትመንት የካፒታል እንደሌለ የሚናገሩት ባለሙያው፣ የካፒታል መሥፈርት አለመቀመጡ ትልቁ ችግሩ ነው ብለዋል። ሦስት ማደያና አንድ ዲፖ ያለው ግለሰብ ከፍተኛ ገንዘብ የሚጠይቀውን ሥራ ለመሥራት በቂ የገንዘብ አቅም ሳይኖረው ወደ ነዳጅ ንግድ እንዲገባ መፈቀዱ ከነዳጅ እጥረት ጋር ለተፈጠሩ ችግሮች አንድ ምክንያት መሆኑን አስረድተዋል።

በተለይ የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ለእነዚህ ኩባንያዎች የ30 ቀናት ዱቤ ይሰጥ የነበረውን አሠራር እየቀነሰ ሲመጣ፣ ኩባንያዎቹ ነዳጁን ገዝተው ለማምጣት የገንዘብ ችግር ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡ በሌላ አነጋገር ነዳጅ ገዝተው ለማሠራጨት አቅም የላቸውም ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ። የመሥሪያ ገንዘብ ችግር አለባቸው፣ ይህ ራሱ ግብይቱ ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው የሚገልጹት ሠርካለም (ዶ/ር)፣

(ወደ ገፅ 4 የዞረ)

# ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ማቅረብ ያልቻሉ ኩባንያዎች በአገር ውስጥ እንዲሸጡ ተጠየቀ

ኢትዮጵያ ከአሜሪካ መንግሥት ታገኘው የነበረው ከኮታና ከቀረጥ ነፃ የንግድ ዕድል (አጎዋ) በመነሳቱ ምክንያት፣ የገበያ ዕድላቸው የተዘጋባቸው የቆዳ ውጤቶች አምራች የውጭ ኩባንዎች ከምርታቸው ውስጥ የተወሰነውን ለአገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት፣ ለኢንቨስትመንት ኮሚሽንና ለገንዘብ ሚኒስቴር ጥያቄ አቀረበ፡፡

ፋብሪካዎቹ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ከመንግሥት ጋር የተስማሙበት ውል፣ የሚያመርቱትን የቆዳ ውጤት ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ የሚል ሲሆን፣ ፋብሪካዎቹም የአሜሪካን ከቀረጥ ነፃ ገበያ ታሳቢ አድርገው ወደ ኢትዮጳያ ገብተዋል፡፡ ይሁንና የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያ ከሰብዓዊ መብት ጥሰት ጋር በተያያዘ ለአጎዋ ተጠቃሚነት የሚያበቁ መሥፈርቶችን አላሟላችም በሚል ተጠቃሚ እንዳትሆን የተጣለው ዕግድ ከእ.አ.አ. ጥር 1 ቀን 2014 ዓ.ም. ተፈጻሚ መሆን ጀምሯል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከዚህ ቀደም የአጓዋ ዕድል በታገዱ 64 በመቶ የሚሆነውን ቆዳና የቆዳ ውጤት ወደ አሜሪካ ለመላክ አስቸጋሪ ሁኔታ መፈጠሩን አስታውቆ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ላለፉት 21 ዓመታት አጎዋን ተጠቅማ በተለይ የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን ወደ አሜሪካ ከቀረጥ ነፃ ስትክል የቆየች ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚመረቱ ጫማዎችና የቆዳ ውጤቶች ውስጥ ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነው መዳረሻው አሜሪካ ነበር፡፡

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ብርሃኑ ፍርጀቦ ለሪፖርተር እንደተናገሩት፣ በኮቪድ-19 እጅጉን ሲፈተኑ የከረሙት ወደ ውጭ ላኪ የቆዳ ውጤት ማምረቻ ፋብሪካዎች፣ አሁን ደግሞ የአጎዋ መታገድ እጅጉን ጎድቶዋቸዋል፡፡ በቆዳ፣ በጫማ፣ በጓንት፣ እንዲሁም ቦርሳና ኮት ባሉ የቆዳ አልባሳትና ዕቃዎች ከተሰማሩ ፋብሪካዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ እየተንቀሳቀሱ ያሉት በአቅማቸው 50 በመቶ በታች ነው፡፡

ሁጃን (Huajian Shoe Factory)፣ ጆርጅ ሹ (George Shoe Ethiopia Plc.) እና ዮባንግ (Youbang Manufacturing Of Shoes Plc) የሚባሉት ትልልቅ ጫማ አምራች የውጭ ፋብሪካዎች ሙሉ ለሙሉ እያመረቱ አይደሉም፡፡ እነዚህ ኩባንያዎቹ ኮቪድ-19 ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ ሲፈተኑ የቆዩ ቢሆኑም፣ አሁን ደግሞ የአጎዋ ዕድል መቋረጡ ሥራ እንዳይጀምሩ አድርጓቸዋል፡፡

ከአጎዋ መቋረጥም ተጨማሪ የቆዳ ውጤቶች ኤክስፖርት ዘርፉ በኮቪድ-19፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነትና ተያይዞ በመጣው የፕሮፖጋንዳ ጦርነት ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡ እንደ አቶ ብርሃኑ ገለጻ፣ በበጀት ዓመቱ ስምንት ወራት ከአጠቃላይ ዘርፉ 51 ሚሊዮን የአሜካ ዶላር ለማግኘት ታቅዶ ማሳካት የተቻለው 27.3 ሚሊዮን ዶላር ያህሉን ነው፣ ይህም የዕቅዱን 53.3 በመቶ የሚሸፍን ነው፡፡ የዘርፉን ዕቅድ በትልቁ የጎዳው በጫማ ኤክስፖርት ላይ ማሳካት የተቻለው 30 በመቶ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ይኼም ከሦስት ትልልቅ ጫማ አምራች ፋብሪካዎች ምርት ማቆም ጋር እንደሚያያዝ አቶ ብርሃኑ አስረድተዋል፡፡

የፋብሪካዎቹ አንደኛው ጥያቄ ሲገቡ የተስማሙበት ውል ተሻሽሎ ለአገር ውስጥ ገበያ ምርታቸውን የሚያቀርቡበት መንገድ የሚቻል እንደሆነ የገለጹት ዳይሬክተሩ፣ ጉዳዩ ውል ማሻሻልን የሚጠይቅ በመሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እንደማይመለስ አስረድተዋል፡፡ ይህንን ጥያቄ መመለስ የሚችሉት ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ገንዘብ ሚኒስቴርና የጠቅላይ ሚኒስተር ጽሕፈት ቤት በመሆናቸው፣ ሚኒስቴሩ ለእነዚህ አካላት ጥያቄውን ማቅረቡን አስረድተዋል፡፡

ከፋብሪካዎቹ ጋር የተገባውን ውሉ የማሻሻል ሥልጣን ያላቸው እነዚህ አካላት በጉዳዩ ላይ ውይይት እያደረጉ መሆኑንና ጥያቄ ዕልባት ለማግኘት ጫፍ ላይ መሆኑን አቶ ብርሃኑ ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካዎቹ ያቀረቡት ጥያቄ የምርታቸውን 50 በመቶ ለአገር ውስጥ ገበያ ለማቅረብ ቢሆንም፣ ይህንን ያህል መጠን ላይፈቀድላቸው እንደሚችል የጠቆሙት አቶ ብርሃኑ «20 በመቶውን እንዲያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል፤» ብለዋል፡፡ ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘ ከዚህ ዕድል ተጠቃሚ የሚሆኑት የቆዳ ምርቶችን ሙሉ ለሙሉ ኤክስፖርት ብቻ ሲያደርጉ የነበሩ ዘጠኝ የቆዳ፣ አራት የጫማና ሁለት የጓንት የውጭ ፋብሪካዎች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከዘርፉ ይገኝ የነበረው ገቢ በአጎዋ ምክንያት እንዳይታጣ ወደ አፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ገበያ የማፈላለግ ሥራ እንደተጀመረ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ሲባል በተለይ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሥራዎችን ለማጠናከርና በሰጥቶ መቀበል መርህ የአገሮቹ ገበያ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡበትና የኢትዮጵያዎቹም የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ለመፍጠር የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች ከአገሮቹ ባለሥልጣናት ጋር ንግግር እያደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25114

# መንግሥት እጁን የታሰረበት ...(ከገፅ 3 የዞረ)

የገንዘብ አቅማቸው ሳይታይ ሥራ ውስጥ መግባታቸው ያመጣው ችግር መሆኑ መታወቅ አለበት ይላሉ፡፡ የዱቤ አገልግሎቱን ለማግኘት በዜሮ ገብተው የሚሠሩ እንደነበሩ፣ በዚህም ትርፍ ያካበቱ እንዳሉ የጠቆሙት ሠርካለም (ዶ/ር)፣ ይህም የአዋጁ ክፍተት በመሆኑ መስተካከል አለበት ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ፣ በተለይ ሕገወጥ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉትን መንግሥት ለመቆጣጠርና ሕግ ለማስከበር ያልቻለው ደግሞ፣ በሕገወጥ ንግድ ውስጥ የተሰማሩ ሰዎች የፋይናንስ ጡንቻ ስላላቸውና የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ሰዎችን በአጋርነት የያዙ በመሆናቸው መንግሥት ሕገወጦቹን በሕግ ለመጠየቅ እንዳልቻለና እጁ እንደታሰረ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለውን ሕገወጥ ተግባር በፀረ ሙስና ኮሚሽን ተይዞ በምን እንደሆነ ባልታወቀበት ሁኔታ እንዲቆም መደረጉንም በአስረጅነት አቅርበዋል፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚፈጠሩ የነዳጅ እጥረቶች እንዲህ ያሉ ችግሮች ሁሉ የሚታዩበት በመሆኑ ነገሩን በመንገድ መበላሸትና መሰል ችግሮች ጋር ብቻ አሳንሶ ማየት ተገቢ አለመሆኑን ባለሙያው ሠርካለም (ዶ/ር) ያመክራሉ፡፡ በጥቅል ሲታይም የእጥረቱ ምንጭ ሙስና መሆኑን መናገር ይቻላልም ብለዋል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍም ሕጋዊ ዕርምጃዎች ላይ በርትቶ መሥራት ውጪ አማራጭ እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡

የነዳጅ ግዥ ሒደት

አገሮች ከውጭ የሚገዙትን ነዳጅ ለማስገባት የተለያዩ ዘዴዎች ይጠቀማሉ፡፡ እንደ ኬንያ ያሉ አገሮች ነዳጅ የሚያስገቡት የውጭ ኩባንያዎች ሲሆን፣ መንግሥት ወቅታዊውን የዋጋ ንረት ተከትሎ ኩባንያዎቹን ከዚህ በላይ መሸጥ አትችሉም ብሎ የዋጋ ጣሪያ በማስቀመጥ ይሠራል፡፡ በኢትዮጵያ ነዳጅ ግዥን የሚፈጽመው መንግሥት ነው፡፡ ነዳጅ የሚያቀርብላትን ኩባንያ ለመምረጥ የሚካሄደው ጨረታ የነዳጅ ዋጋን አያካትትም፡፡ የጨረታ ዋጋው ፕሪሚየር ነው፡፡ ጨረታው ፍሬት፣ የራሱን የፋይናንስ ኮስት ጨምሮ በሚቀርበው ዋጋ መሠረት ውድድር ተደርጎ ይመረጣል፡፡ ለምሳሌ ከነዳጅ ዋጋ ሌላ በአንድ በርሜል አሥር ዶላር ወይም አሥራ አምስት ዶላር አቀርባለሁ ይላል፡፡ በዚህ ነው ተጫራቾች የሚወዳደሩት፡፡ ስለዚህ የወሩ አማካይ ዋጋ ይህ ነው ተብሎ በዚያ ዋጋ ላይ የተጫራቹ ዋጋ ታክሎ ነዳጁን ያቀርባል፡፡

ስለዚህ 60 እና 70 ዶላር በሚሸጥበት ወቅት ይህ ዋጋ በወር ውስጥ ተሠልቶ አማካይ ዋጋው 65 ዶላር ከሆነ ኢትዮጵያ ውል ከገባችው ኩባንያ አማካዩን 65 ብር ዋጋና ኩባንያው አሸናፊ የሆነበትን አሥር ዶላር በመጨመር 75 ዶላር ትከፍላለች ማለት ነው፡፡ አሁን ደግሞ የነዳጅ ዋጋ 140 ዶላር ደርሷል፡፡ ስለዚህ ባለፈው አንድ ወር የነዳጅ ዋጋ አማካዩ 135 ዶላር ቢሆን፣ ኢትዮጵያ አንዱን በርሜል ዶላር ወደ አገር ለማስገባት የምታከፋፍለው 145 ዶላር ይሆናል፡፡ ባለፈው አንድ ወር እንዲህ ባለው መንገድ ተሠልቶ ግዥው ተፈጽሟል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ሳቢያ ያልታሰበ ተጨማሪ ወጪ እንድታወጣ አስገድዷታል፡፡ ስለዚህ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረገው የነዳጅ ጭማሪ ኢትዮጵያን ተጨማሪ አሥር ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ እንድታወጣ ወይም እንድትከስር አድርጓል፡፡ ይህንን መንግሥት ሸፍኖ ዋጋ ጭማሪ ሳያደርግ ሽያጭን እያከናወነ እንደሚገኝ ከኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡

የነዳጅ ዋጋ ላይ ጭማሪ ይደረጋል? አደጋውስ?

የሰሞኑ የዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አገሮች የነዳጅ ዋጋ ትርፋቸውን እንዲጨምሩ አስገድዷል፡፡ ለነዳጅ የሚያወጡት ወጪ በመጨመሩ፣ እንደ አገሩ ተጨባጭ ሁኔታ የችርቻሮ መሸጫቸው ላይ ጭማሪ በማድረግ እንዲሸጥ ወስነዋል፡፡ ይህ የመንግሥት ውሳኔ ነው፡፡ «የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ይደረጋል ወይ?» የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ታደሰም፣ ይህ የመንግሥት ውሳኔ ነው ይላሉ፡፡ መንግሥት ሁኔታውን እያየ የዋጋ ንረትና የመሳሰሉትን ለማየት ጭማሪው ቢደረግ ምን ሊያስከትል ይችላል? የሚለውን ሁሉ በማየት የሚወሰነው ይሆናል፡፡ መንግሥት ምንም ይወስን ምን ኅብረተሰቡ ነዳጅን በቁጠባ የመጠቀም ባህሉን ማሳደግ አለበት ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ታደሰ ገለጻ፣ አሁን ላይ ነዳጅ ላይ ዋጋ ቢጨመር ኅብረተሰቡ ይጎዳል፡፡ ዋጋ ባልተጨመረበት ሁኔታ ኅብረተሰቡ ደግሞ አጠቃቀሙን በማስተካከል ወጪን መቀነስ ኃላፊነት አለበትም ብለዋል፡፡

ለምሳሌ አሁን ላይ ለነዳጅ በወር 250 ሚሊዮን ዶላር እየወጣ ነው፡፡ ስለዚህ የምንጠቀምበትን ነዳጅ በመቀነስ ወጪያችን እንዲቀንስ በማድረግ በዚህ ቅናሽ ለሌሎች ምርቶች መግዣ እንዲውል ሁሉም መተባበር አለበት ብለው፣ አሁን ላይ ጭማሪ ያለ መደረጉንም መጥቀስ ያስፈልጋል፡፡

አገር መቀጠል የምትችለው ሁሉም ሲተባበር ነው፡፡ በሥነ ልቦና መዘጋጀትም ያስፈልጋል፡፡ ሰሞኑን በአውሮፓ ነዳጅ አጠቃቀማችሁን አስተካክሉ፣ ቆጥቡ እያሉ መሆኑን ፈረንሣይን በምሳሌነት የጠቀሱት አቶ ታደሰ እዚህም አጠቃቀማችንን ማስተካከል ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ ሠርካለም (ዶ/ር)፣ ደግሞ አሁን ባለው ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ የነዳጅ ጭማሪ ማድረግ ተገቢ ያለመሆኑን ነው፡፡

ጦርነቱ ምን ያህል ጉዳት አደረሰ ?

እንደ ሌላው የዓለም ክፍል ሁሉ፣ በሩሲያና በዩክሬን መካከል በተፈጠረው ጦርነት ኢትዮጵያ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አስገድዷል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የጨመረው የነዳጅ ዋጋ ኢትዮጵያ ላይ የፈጠረውን ተፅዕኖ በተመለከተ አቶ ታደሰ የዋጋ ጭማሪው ኢትዮጵያን እስከ 10 ቢሊዮን ብር እንድታጣ አድርጓል፡፡ ይህ ኪሳራ እንደማለት ነው ያሉት አቶ ታደሰ፣ አሁን ኢትዮጵያ ነዳጅን በምታስገባበት ዋጋ ተሠልቶ ቢሸጥ አንድ ሌትር ቤንዚን ትክክለኛ ዋጋው 76 ብር እንደነበረበትም ጠቅሰዋል፡፡ አሁን ግን በአዲስ አበባ 37.74 ብር እየተሸጠ መሆኑ ምን ያህል ትልቅ ልዩነት እንዳለው መገመት ይቻላል፡፡ የዓለም ዋጋ ከእንግዲህም እየቀጠለ የሚሄድ ከሆነ አደጋ ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን እውነት ኅብረተሰቡ በደንብ ሊያጤነው ይገባል፡፡ በተወሰነ ደረጃ ይህንን መካፈል ቢቻል እንኳ ቀላል ነገር አይደለም፡፡

በዝቅተኛ ዋጋ ነዳጅ የሚሸጥበት አገር ኢትዮጵያ

ዓለም አቀፉ የነዳጅ ዋጋ ወደ 140 ዶላር ደርሷል፡፡ በእያንዳንዱ የዓለም አገር ነዳጅ ዋጋ በተለያየ መጠን ጭማሪ አድርገዋል፡፡ በኮታ ነዳጅ እያደሉ ያሉ አገሮች አሉ፡፡ እንደ ፈረንሣይ ያሉ አገሮች ደግሞ ማንኛውንም የኃይል ምንጮችንና ነዳጅን በቁጠባ እንዲጠቀሙ በይፋ አውጀዋል፡፡ ይህንን እወጃ ያደረጉ ደግሞ በነዳጅና የኃይል አቅርት ዋጋ ላይ ጭማሪ አድርገው ነው፡፡ ይህ በኢትዮጵያ አልተደረገም፡፡ በዚሁ ይቀጥላል ማለት ግን እንዳልሆነ ይታመናል፡፡ እስካሁን ባለው ኢትዮጵያ ነዳጅ የችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ግን ከዓለም አቀፍ ዋጋ አንፃር ሲመዘን እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የችርቻሮ የነዳጅ ዋጋ አነስተኛ የሆነው በመንግሥት የሚደጎም በመሆኑ ነው፡፡

በሌሎች አገሮች የመሸጫ ዋጋውን ትተን የጎረቤት አገሮችን ወቅታዊ ዋጋ በብር ተመንዝሮ ሲታይ፣ በአንድ ሌትር ቤንዚን በኤርትራ 70 ብር፣ በኬንያ 50 ብርና በጂቡቲ 120 ብር እየተሸጠ መሆኑ የኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ ሽያጭ ምን ያህል ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል ተብሏል፡፡

የዓለም አቀፉ ድርጅት ሰሞናዊ መረጃ እንደሚሳየውም፣ ከ220 በላይ ከሚሆኑ አገሮች የአንድ ሌትር ቤንዚን ከአንድ ዶላር በታች ከሚሸጥባቸው ጥቂት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗን ያመለክታል፡፡

በዚህ መረጃ መሠረት በዓለማችን ለአንድ ሌትር ቤንዚን ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልበት ቬንዝዌላ ስትሆን፣ የአንድ ሌትር ቤንዚን 1.27 ሳንቲም ነው፡፡ ከፍተኛ ዋጋ የሚጠየቅባት አገር ደግሞ ሆንግ ኮንግ ስትሆን በሆንግ ኮንግ የአንድ ሌትር ቤንዚን ወይም 146 ብር ነው፡፡ በአፍሪካ ዝቅተኛ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ ያላት አገርም ኢትዮጵያ ናት፡፡

የነዳጅ ዋጋ ጭማሪንና የዋጋ ንረት

የነዳጅ ዋጋ መጨመርና መቀነስ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ነዳጅ ሁሉንም ነገር የሚነካካ መሆኑም ገበያ ላይ ሊፈጥረው የሚችለው ተፅዕኖ አለ፡፡ የኢኮኖሚ ባለሙያዎችም ይህንኑ በሚገባ ይተነትናሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገርናቸው አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ ግን ለየት ያለ ምልከታ አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ሲደረግ በገበያ ላይ የሚያስከትለው የዋጋ ለውጥ ብዙም አይደለም የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይህም ፈፅሞ የነዳጅ የጭማሪው መጠን ያላገናዘበ እንደሆነ ይሞግታሉ፡፡፡

ለምሳሌ እንደ ብሔራዊ ስታስቲክስ ያሉ ተቋማት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከ100 (ቤቶች) ሐውስ ሆልድ መረጃ ይጠይቃል፡፡ የአስቤዛ ዋጋ ነው የሚጠይቀው፡፡ ለስኳር፣ ለዘይት፣ ለጤፍና ለሽንኩርት ይህንን ያህል አወጣለሁ የሚል መረጃ ይይዛል፡፡ በኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ ከ100 ሐውስ ሆልድ ለነዳጅ ወርኃዊ ወጪዬ ይህንን ያህል ነው የሚል ላታገኝ ትችላለህ፡፡ ከመቶ አንድ እንኳን ላይገኝ ይችላል፡፡ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ያለባት አገር ውስጥ ያለው 1.4 ሚሊዮን መኪና ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ መኪና አለ የሚባል አይደለም፡፡ በዚህ የዋጋ ንረትን ስትመዝን አስቤዛ ውስጥ የሌለውን ነገር አስቀምጠህ የዋጋ ንረት ተብሎ መጠቀስ አለበት ብለው አያምኑም፡፡

የነዳጅ ዋጋ ላይ የሚደረግ የተወሰነ ጭማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚወራለትን ያህል የዋጋ ንረት አያስከትልም የሚሉት እኚሁ ባለሙያ፣ አውሮፓና አሜሪካ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ በትክክል ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ ለነዳጅ በወር ይህንን ያህል ወጪ አወጣለሁ የሚሉ ብዙ በመሆናቸው ነው ይላሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፅዕኖው ትንሽ ነው ይላሉ፡፡  ኢትዮጵያ ውስጥ

(ወደ ገፅ 5 ዞሯል)

## የሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን ለማዘመንና የፖሊስተር ጨርቅ ለማምረት የተጀመረው ጥረት

ቀደምት ከሚባሉ የኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች መካከል አንዱ የሆነውን ሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን ከመንግሥት የገዛው ሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርክ አክሲዮን ማኅበር የፋብሪካውን ነባር ማሽነሪዎች በማስወገድ አዳዲስ መሣሪያዎችን በመትከል የጨርቃ ጨርቅ ምርቶችን ለማምረት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

ሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርክ አክሲዮን ማኅበር የቆዩ ማሽነሪዎችን አስወግዶ አዳዲስ ማሽነሪዎችን ለመትከል ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የመደበ መሆኑን የገለጸ ሲሆን፣ ፕሮጀክቱም በመካሄድ ላይ መሆኑንና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ ወደ ምርት እንደሚገባ አስታውቋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ፋብሪካውን በአዲስ የማምረቻ መሣሪያዎች የመተካቱ ሥራ በመጠናቀቅ ላይ እንደሆነም ተገልጿል። ፋብሪካውን በአዲስ መልኩ ለማደራጀት፣ የመሣሪያ ተከላውና ሕንፃውን ለማደስ ሥራ እስካሁን ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ መደረጉን የኩባንያው ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ አህመድ አብዳሩፍ ገልጸዋል፡፡

ፋብሪካውን ለማዘመንና ቀደም ሲል በመንግሥት ይተዳደር በነበረበት ወቅት ይመረቱ የነበሩ የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶችን በሙሉ ለመቀየር መታቀዱን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ አዳዲስ ማሽነሪዎችን በመትከል ሁለት ዓይነት አዲስ ምርቶች እንደሚመረቱ አስታውቀዋል።

አዲስ ማሽኖች ከተተከሉ በኋላ ፋብሪካው ሁለት የምርት መስመሮች የሚኖሩት ሲሆን፣ በአንደኛው የምርት መስመር «ክሊኒከር» የተባለውን ክር እንደሚመረት ተናግረዋል። ለዚህም የሚሆኑ አዳዲስ ማሽነሪዎች ተከላ መጠናቀቁን ሰሞኑን ፋብሪካው በተጎበኘበት ወቅት ተገልጿል፡፡

በኢንዱስትሪ መንደሩ ሁለተኛ የምርት መስመር ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ደግሞ በተለየ ሁኔታ የፖሊስተር ምርት እንደሚመረትበት ተገልጿል። ለዚህ የምርት መስመር የሚያገለግሉ የአዳዲስ ማሽነሪዎች ተከላ እየተከናወነ ሲሆን፣ ተከላውን ለማጠናቀቅ የሚያግዙ የተወሰኑ ቀሪ ዕቃዎችን በመግጠም ለሥራ ዝግጁ ይሆናል ተብሏል፡፡

እነዚህ ቀሪ ዕቃዎች በአሁኑ ወቅት ጂቡቲ የሚገኙ በመሆኑ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ገብተው ከተገጠሙ በኋላ ሁለቱም የምርት መስመሮች በአጭር ጊዜ ወደ ምርት እንደሚገቡ ይጠበቃል።

በእነዚህ የፋብሪካው አዳዲስ ማምረቻዎች የሚመረቱት ምርቶች ለኢትዮጵያ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ግብዓቶችን የሚያመርቱ ይሆናል ተብሏል፡፡

እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፣ በተለይ የፖሊስተር ጨርቅ ያመርታል ተብሎ የሚጠበቀው  የፋብሪካው የማምረቻ መስመር ለምርት ግብዓትነት የሚጠቀምበትን ዋነኛ የጥሬ ዕቃ ግብዓት ከአገር ውስጥ የሚጠቀም ይሆናል፡፡ የፖሊስተር ምርቱን ለማምረት ግብዓት የሚሆኑት ጥሬ ዕቃዎች አገልግሎት የሰጡና የወዳደቁ የፕላስቲክ ምርቶች መሆናቸውን ኃላፊው ገልጸዋል።

አነስተኛ የጥሬ ዕቃ ከውጭ የሚገባ ቢሆንም፣ አብዛኛው ጥሬ ዕቃ አገልግሎት ላይ የዋሉ የፕላስቲክ ምርቶች ታጥበውና ተፈጭተው በግብዓትነት እንደሚውሉ ኃላፊው አስረድተዋል። በዚህ የምርት መስመር በቀን አሥር ቶን ፖሊስተር የማምረት አቅም ያለው መሆኑ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የክር ማምረቻው ደግሞ በቀን ሰባት ቶን የማምረት አቅም እንደሚኖረው አስረድተዋል። እነዚህ በፋብሪካው የሚመረቱ አዳዲስ ምርቶች ለአገር ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ብቻ ሳይሆን፣ ለውጭ ገበያም የሚቀርቡ ናቸው ተብሏል፡፡

ኩባንያው የሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብካሪን በአዲስ ከማደራጀት ባለፈ፣ በዚያው የሐዋሳ የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውስጥ ባለው ሰፊ ቦታ በኢትዮጵያ የመጀመርያ የተባለውን የግል የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርክ ግንባታ እያካሄደ ነው፡፡ ፓርኩ እየተገነባበት ያለው አጠቃላይ የቦታ ስፋት 25 ሔክታር ሲሆን፣ በ11 ሺሕ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚያርፉ 14 ሼዶች እንደሚነቡም ታውቋል።

ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ይጠይቃል የተባለው ይህ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ግንባታ ሥራ መጀመርያ ላይ ታስቦ የነበረው በሁለት ቢሊዮን ብር ግንባታውን ለማከናወን ነበር፡፡ የግንባታው የመሠረተ ድንጋይ ከተቀመጠ በኋላ ግን የዲዛይን ለውጥ ተደርጎ የበለጠ ለማስፋፋት መወሰኑን ለማወቅ ተችሏል።

የዲዛይን ለውጥ መደረጉ የግንባታ ሥራው እንዲዘገይና የግንባታ ወጪውንም ወደ አራት ቢሊዮን ብር ያሳደገው መሆኑን የኩባንያው ሥራ አስፈጻሚ ገልጸዋል፡፡ ከ14ቱ ሼዶች ሌላ የኢንዱስትሪ ፓርኩ የአንድ መስኮት አገልግሎት መስጫ ማዕከል፣ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ የመኖሪያ አፓርትመንቶችና የውኃ ማጣሪያ ማዕከሎች እንሚገነቡ ተገልጿል።

የግንባታ ሥራውን የሚያከናው ነው «ሲኖማ» የተባለው የቻይና ኩባንያ ሲሆን፣ ይህ ኩባንያ ከዚህ ቀደም ወደ አራት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባት ይታወቃል፡፡ የሐዋሳ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርክ የግንባታ ሥራ በአሁኑ ወቅት 37 በመቶ የተከናወነ ሲሆን ከዲዛይን ለውጡ ባሻገር፣ በዋና ዋና የግንባታ ግብዓቶች ላይ የታየው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪና አጋጥሞ የነበረው የውጭ ምንዛሪ እጥረት አጠቃላይ ግንባታው በታሰበው ፍጥነትና በዕቅዱ መሠረት እንዳይጓዝ ተፅዕኖ ማድረጋቸው ተጠቅሷል፡፡

በተለይም የብረታ ብረትና የሲሚንቶ ምርት አቅርቦት ላይ የተከሰተው እጥረትና ዋጋ መናር ፕሮጀክቱ በተፈለገው ፍጥነት እንዳይከናወን ምክንያት መሆናቸውን የገለጹት ሥራ አስፈጻሚው፣ ይህም ቢሆን ሥራው ሳይቋረጥ እየተሠራ በመሆኑ ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ እንደሚያልቅ ገልጸዋል። የኩባንያው ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሕይወት ታደሰም ይህንኑ አረጋግጠዋል።

ግንባታውን ለማፋጠንም የስቲል ስትራክቸርና የኤሌክትሪክ ሥራዎች ምርት እንዲመረት ከአንድ የቻይና ኩባንያ ጋር ውል ተገብቶ በአሁኑ ወቅት የምርት ሥራ በመካሄድ ላይ መሆኑን የፋብሪካው ኃላፊዎች ገልጸዋል።

በመሆኑም የሚመረቱትን ብረታ ብረትና ስቲል ስትራክቸር ገጣጥሞ ለሥራ ዝግጁ ማድረጉ ጥቂት ወራትን ብቻ የሚፈርጅ ይሆናል ተብሏል፡፡ ይህንን ሥራ በቶሎ ለማጠናቀቅ ግን የአገር ውስጥ የግንባታ ግብዓቶች አቅርቦት ችግርና ቀሪውን የግንባታ ወጪ ለማጠናቀቅ ከባንክ ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀው ብድር በቶሎ መለቀቅ ወሳኝ መሆናቸውን ከኃላፊዎቹ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል፡፡

እስካሁን የፓርኩን ግንባታ ወጪ የኩባንያው በራሱ የገንዘብ ምንጭ እሸፈነ መቆየቱን የሚገልጹት የኩባንያው የሥራ ኃላፊዎች፣ ለቀሪው ግንባታ የሚሆነውን ተጨማሪ ፋይናንስ ከባንክ ለማግኘት ታቅዶ የነበረ ቢሆንም፣ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ብድር እንዳይሰጡ በመመርያ ጥሎት የነበረው ዕግድ እንቅፋት ሆኖ መቆየቱን ገልጸዋል፡፡

አሁን በባንክ ብድር ላይ የተጣለው ዕግድ በመነሳቱና ይኼንን የሚያህል ግዙፍ ፕሮጀክት በራስ አቅም ብቻ መገንባት አዳጋች በመሆኑ፣ ለአንድ የመንግሥት ባንክ የብድር ጥያቄ አቅርበው ውጤቱን እየጠበቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኩ ግንባታ ሲጠናቀቅ የሚፈጠሩትን 14 የማምረቻ ሼዶች ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ የጨርቃ ጨርቅ ኩባንያዎች እንደሚከራዩ ለማወቅ ተችሏል።

የቀድሞውን ፋብሪካ በአዲስ ማሽነሪዎች ተክቶ ወደ ሥራ ሲገባ ለ1,200 ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር ይሆናል ተብሏል፡፡ በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ፓርኩ ሥር የሚገነቡት 14 ሼዶች ሙሉ በሙሉ በአምራቾች ሲያዙ ደግሞ ከ25 እስከ 30 ሺሕ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ተገምቷል፡፡

ኩባንያው የሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካን በግማሽ ሚሊዮን ብር ከመንግሥት የተገዛ መሆኑ ይታወሳል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25156

## መንግሥት እጁን የታሰረበት ...(ከገፅ 4 የዞረ)

ተፅዕኖው ትንሽ ነው ይላሉ፡፡ በኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ተፅዕኖው የጎላ ነው የሚባልበት ምክንያት በደንብ ቢፈተሽ መልሱ ሊገኝ ይችላልም ይላሉ፡፡ በነዳጅ ላይ የዋጋ ማስተካከያ ወይም ጭማሪው መጠንና ይህንን ጭማሪ ሰበብ አድርጎ በሌሎች ምርቶች ላይ የሚደረገው ጭማሪ በፍፁም የሚጣጣም ያለመሆኑን ያመጣው ችግር ነው ያሉት እኚሁ የኢኮኖሚ ባለሙያ፣ ችግሩ ይህንን ያህል ነዳጅ ዋጋ መጨመሩ በሌሎች ምርቶች ላይ ምን ያህል ዋጋ ሊያስጨምር ይችላል ብሎ የሚከታተል አካል ባለመኖሩ የተፈጠረ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ያለውን ነገር በደንብ መቆጣጠር ስለማንችል፣ የግብይት ሥርዓቱን የሚቆጣጠር ባለቤት ስለሌለው ወይም ዘመናዊ ባለመሆኑ ነዳጅ ሲጨምር በሌሎች ምርቶች ላይ የሚጨመረው ዋጋ በሰበብ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህን ሙግታቸውን በምሳሌ ለማጠናከር በእህል ገበያ የሚታየውን ጭማሪ ነው፡፡ በነዳጅ ጨመረ ሰበብ ዋጋውን ያስወድዳል የሚባለው ምርቱን ለማመላለስ ተሽከርካሪዎቹ የሚፈጁት የነዳጅ ዋጋ ጨመረ በሚል ነው፡፡ በአንድ ጉዞ አንድ የጭነት መኪና በነዳጅ ጭማሪ ሳቢያ 100 ብር ከጨመረበት የተጫነው እህል ጤፍ ቢሆን የጤፍ ዋጋ ላይ 500 ብርና 600 ብር ይጨምራል፡፡ ስለዚህ ይህ ችግር የሚፈጠረው በአገር ደረጃ እንዲህ ያለውን መሠረታዊ ጉዳይ የሚቆጣጠር አካል ካለመኖሩ ጋር የተያያዘ ነው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ምን ያህል ለውጥ ያመጣል? ብሎ አሥልቶ ይህ እንዲህ መሆን አለበት ብሎ የሚያስቀምጥ የለም፡፡

ሥርካለም (ዶ/ር) ግን በዚህ ሐሳብ አይስማሙም፡፡ የነዳጅ ጭማሪ ገበያ ውስጥ የዋጋ ለውጥ ያመጣል፣ ሁሉንም ይነካካል ብለዋል፡፡ ነገር ግን በተወሰነ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ነዳጅ ጨመረ ተብሎ የሚደረጉ አንዳንድ ጭማሪዎች ግን ቁጥጥር ሊረግባቸው ይገባል እንጂ ተፅዕኖ ትንሽ ነው ማለት እንደማይቻል አመላክተዋል፡፡ ችግሩ ከአጠቃላይ አሠራሩ ላይ ያለ ነው፡፡ የሕግ ክፍተት በመኖሩ የመቆጣጠሪያ ሥልት ስለሌለም የሚፈጠር ነው፡፡

ይህም ችግር አለ

በዚህ ዘርፍ ያለው ችግር ከነዳጅ ባለድርሻ አካላት ጭምር ሮሮ የሚቀርብበት ነው፡፡ ትርፍ ህዳግ አተማመን ጥያቄ ይነሳበታል፡፡ ተገቢ ዋጋ አልተሰጠኝም የሚሉ የዘርፉ ተዋንያኖች አሉ፡፡ ወቅቱን ጠብቆ ማስተካከያ እየተደረገልን አይደለም የሚለው አቤቱታ በሁሉም ዘርፍ ይታያል፡፡ ሰሞኑንም የኢትዮጵያ ነዳጅ አመላላሽ ባለንብረቶች ማኅበር ይህንኑ አንፀባርቀዋል፡፡ የማኅበሩ ሊቀመንበር እንደገለጹት፣ በ3,200 የሚደርሱ ቦቴዎች ከአርባ በላይ በሚሆኑ የነዳጅ ኩባንያዎች ውስጥ ተመዝግበው እየሠሩ የሚገኙ ቢሆንም ብዙ ችግሮች እንዳለባቸው ነው፡፡

«የመኪኖች ስታንዳርድ በመጨመሩ፣ የብር የመግዛት አቅም በመዳከሙ የተሽከርካሪ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በመጨመሩ ምክንያት በአሁኑ ወቅት የተደረገው ኢንቨስትመንት እስከ 20 ቢሊዮን ብር እንደሚደርስ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

እነዚህ ተሽከርካሪዎች በዓመት ጭነት የማንሳት አቅምም ከስድስት ሚሊዮን ቶን ይገመታል፡፡ የነዳጅ ማመላለሻ ሥራው በነፃ ገበያ የሚመራ ባለመሆኑ እየጎዳ ነው ብለዋል፡፡ በመንግሥት የሚወሰነው ክፍያቸው ማስተካከያ የማይደረግለት መሆኑ ብዙዎችን ከሥራ እያስወጣ ነው፡፡ ከሁለት ዓመታት ወዲህ የውጭ ምንዛሪ እጥረትና የብር የመግዛት አቅም መዳከም ደግሞ  ተሽከርካሪዎችን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ዋጋ በየቀኑ እየናረ መምጣቱን ታሳቢ ያደረጉ ማስተካከያ በወቅቱ ስለማይደረግ ችግር ውስጥ መግባታቸውን አመልክተዋል፡፡

በዚህም ምክንያት ከ20 በመቶ በላይ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ከሥራ ውጪ ሆነዋል፡፡ በርካታ ተሽከርካሪዎችም የሥራ ዘርፋቸውን የቀየሩ ሲሆን፣ ባለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ ወደ ነዳጅ ማመላለሻ የተቀላቀሉት በጣም አነስተኛ ናቸው፡፡ ዘርፉ ከመለዋወጫ ዋጋ መናር ጋር ተያይዞ ካሉ ችግሮች ባሻገር በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው ተብሏል፡፡

እንዲህ ያሉ ችግሮችን የገለጸው በማኅበሩ ችግሬቹ ካልተፈቱ ሥራ አቆማለሁ የሚል ውሳኔ እስከማሳለፍ ደርሷል፡፡ ይህ ውሳኔ ደግሞ ዘርፉ ውስጥ ያሉ ችግሮችን ያብሰዋል፡፡ ብዙዎች እንዲህ ያለውን ውሳኔ ለምን ወሰኑ የሚል ጥያቄ እየቀረቡ ቢሆንም ማኅበሩ ደግሞ ችግራችን ከአቅማችን በላይ ሆኗል ይላል፡፡

መፍትሔውስ

ነዳጅ ፖለቲካል ኮሜዲቲ ነው የሚሉት ሥርካለም (ዶ/ር)፣ የኢትዮጵን የነዳጅ ችግር ለመቅረፍ ዘላቂ የሚባለው መፍትሔ ሪፋይነሪ መገንባት ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ብዙ ጠቀሜታ አለው፡፡ አሁን የተጣራውን ማምጣት ውድ ነው፡፡ ስለዚህ ወደፊት ኢትዮጵያ ነዳጅ ታገኝበታለች ለሚባል አካባቢ ይህንን ማጣሪያ መገንባት ይቻላል፡፡ ይህ ካልሆነ ለኢትዮጵያ አማካይ የሚባል በተለይ ማጣሪያውን መገንባት እጅግ አዋጭ ይሆናል፡፡ ሌላው መተግበር ያለበት ደግሞ ፖቴንሺያል ፔትሮሊየም አምራቾች ከሆኑ አገሮች ጋር ስትራቴጂካዊ ማኅበር መፍጠር ነው፡፡

ለምሳሌ ደቡብ ሱዳን አንዷ ብትሆን ትችላለች፣ ከሱዳን ጋር ስትራቴጂክ ማኅበር መፍጠር ቢቻል ቅርብ ስለሆነ እጥረት ቢፈጠር እንኳን በቶሎ ሊገኝ ይችላል፡፡ እንዲህ ያለው ስምምነት ባለቤትነትንም የሚያጠቃልል ስለሚሆን ወጪን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ ይቻላልና ከእሳት ከማጥፋት ባለፈ ዘላቂ ነገሮች መታሰብ እንደሚኖባቸው አመልክተዋል፡፡ ሕጎቻችንን መፈተሽ ሙስናን ማስወገድና በዚህ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎችን መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የነዳጅ ጉዳይ መሠረታዊ ስለሆነ ይህንን የሚመለከቱ ሥራዎች በባለሙያዎች መሠራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ ችግሩን ለማቃለል አንድ መፍትሔ ነው ያሉት ሥርካለም (ዶ/ር)፣ ያለፈውም ሆነ ይህም መንግሥት ትልቁ ችግሩ አድራጊ ፈጣሪው ካድሬው መሆኑ በማለት ሥራው ለባለሙያው መስጠት አለበት ብለዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25134

## የአበባ ምርት የመላኪያ ዋጋን የሚወስን መመርያ ወጣ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአበባ የወጪ ንግድን ለመቆጣጠርና የአበባ ላኪዎች የሚሸጡበትን ዝቅተኛ ዋጋ ገደብ ያስቀመጠ አዲስ መመርያ አወጣ፡፡ በባንኩ በመመርያ መሠረት ከተጠቀሰው ዋጋ በታች መሸጥ የሚያስጠይቅ መሆኑንም አመልክቷል፡፡

ከዓርብ መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል በተባለው መመርያ መሠረት፣ ሆለታና ዓለም ገና አካባቢ የሚመረቱ የደጋ የአበባ ምርቶች በኪሎ ግራም 4.2612 ዶላር፣ የሰመር አበባ ደግሞ 4.7822 ዶላር መሸጥ እንዳለበት ገደብ አስቀምጧል፡፡ በተመሳሳይ እንደ ደብረ ዘይት (ቢሾፍቱ) ባሉ ወይና ደጋ አካባቢዎች የሚመረቱ የአበባ ምርቶች ደግሞ 4.3340 ዶላር ዋጋ የተቀመጠላቸው ሲሆን፣ በዚሁ አካባቢ የሚመረቱ የሰመር አበቦች ደግሞ ከ4.547 ዶላር በታች መሸጥ እንደሌለባቸው በመመርያው ተመላክቷል፡፡

ቆላ አካባቢ የሚመረቱ የሮዝ አበባ ምርቶች በኪሎ ግራም 4.6602 ዶላር፣ የሰመር አበባዎች ደግሞ ከ6.3699 ዶላር በታች መሸጥ እንደሌለባቸው የደነገገው ይህ መመርያ፣ ቁርጥራጭ የአበባ እንቡጦች ደግሞ የሚሸጡ ላኪዎች ከገዥው ጋር ባደረጉት ውል መሠረት የሚሸጡ ይሆናል ብሏል፡፡ ይህም የግብይት ኮንትራቱን በማቅረብ የሚከናወን እንደሆነ አስታውቋል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ አብዛኛዎቹን የአበባ ላኪዎች ያላስደሰተ እንደሆነ እየተነገረ ነው፡፡

በዚህ መመርያ ዙሪያ ያነጋገርናቸው አንዳንድ የአበባ ላኪዎች፣ መመርያው በዚህ ሰዓት መውጣቱ ተገቢ ያለመሆኑንና የአገሪቱን የአበባ የወጪ ንግድ ሊጎዳ ይችላል የሚል ሥጋት አሳድሮባቸዋል፡፡ መመርያው በአግባቡ ተጠንቶ የቀረበ እንደማይመስላቸው የሚያመላክቱት ላኪዎቹ፣ ብሔራዊ ባንክ ይህንን መመርያ መልሶ እንዲያይላቸው የሚጠይቁ መሆኑን ሳይገልጹ አላለፉም፡፡ በተለይ የአበባ ዋጋ አሁን እየቀነሰ ባለበት ወቅት ባንኩ ባወጣው መመርያ መሠረት ለመሸጥ ይከብዳል ይላሉ፡፡ በመመርያው መሠረት በተጠቀሰው ዋጋ ካልሸጡ ላኪዎቹ በቀጣዩ ወር ላይ መላክ አይችሉም የሚል ድንጋጌ በመመርያው መካተቱም የአበባ ወጪ ንግድ ላይ ተፅዕኖ የሚፈጥር ሊሆን ይችላል የሚል ሥጋታቸውንም ገልጸዋል፡፡ እስካሁን የአበባ የወጪ ንግድን በተመለከተ ብዙ የምርት ዓይነቶች ከአራት ዶላር በታች መሸጥ የማይችሉ እንደነበር የተለገጸ ሲሆን የአሁኑ መመርያ ግን ለላኪዎች ይከብዳል ተብሏል፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25112

## የነዳጅ ስርጭት ችግር የሚፈጥሩ የነዳጅ ማደያዎችን እንደማይታገስ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አሳሰበ

ቢሮው በየጊዜው በሚስተዋለው የነዳጅ እጥረት ዙሪያ በከተማው ካሉ የነዳጅ ማደያ ባላቤቶች ጋር ውይይት አድርጓል፡፡

በዚህም መንግሥት በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከሚያስገባቸው ምርቶች መካከል ነዳጅ አንደኛው መሆኑን ገልጾ የአቅርቦት ችግር እንደሌለ ነገር ግን ከስርጭት ጋር ተያይዞ እጥረት መከሰቱ ለማወቅ ተችሏል ብሏል።

ሆኖም ከስርጭት ጋር ተያይዞ አንዳንድ ማደያዎች የሚፈጥሩትን እንግልትና አሻጥር ፊር ለማስያዝ ጠበቅ ያለ እርምጃ እንደሚወስድና ብልሹ አሰራርን እንደማይታገስ ቢሮው ገልጿል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አደም ኑሪ ያልተገባ ጥቅም በመፈለግ እጥረቱን በሚያባብሱ የነዳጅ ማደያዎች ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ተናግረዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመከላከል የነዳጅ አቅርቦትን በማሳደግ እና ቁጥጥሩን በማጠናከር ሌሊት ነዳጅ በሚሸጡት ላይ የመጠን ማሻሻያ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

በዘመናዊ የመረጃ ዘዴ ማደያዎች እለታዊ መረጃን ለቢሮው እንዲያሳውቁ ማድረግ የሚያስችል አሰራር ለመዘርጋት የጋራ መግባባት ላይ መደረሱን የከንቲባ ጽሕፈት ቤት መረጃ አመላክቷል፡፡

በህገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ በፈጠሩና በምሽት በበርሜል ነዳጅ ሲሸጡ የተገኙ ሦስት ማደያዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰዱም ተነግሯል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.youtube.com/watch?v=w65aOJZ-CJM

## የባንኮች ብድር አሰጣጥን ይቀይራል የተባለው ብሔራዊ መታወቂያ




በኢትዮጵያ ይተገበራሉ ተብለው ከታቀዱ በርካታ ውጥኖች መካከል ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው ተብሎ የሚታመንበት ብሔራዊ መታወቂያ አንዱ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን መታወቂያ ለሁሉም ዜጎች በማዘጋጀት ለመስጠት ሳይችል ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

ዜጎች ማንነታቸውን የሚለይ ባለ አሥራ ሁለት ዲጂት መለያ ያለው ብሔራዊ መታወቂያ እንዲኖራቸው ለማስቻል በመንግሥት ደረጃ ከታቀደ ከአሥር ዓመታት በላይ ተቆጥረዋል፡፡ አንዳንዶች ውጥኑን እስከ 20 ዓመት ዘለግ ያደርጉታል፡፡ በእነዚህ ረዥም ዓመታት ውስጥ ግን የብሔራዊ መታወቂያ ጉዳይ በቅርቡ ይተገበራል ከሚል መረጃ ውጪ በተግባር ሊቀየር አለመቻሉ ብዙ እያነጋገረ ቆይቷል፡፡

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ሥር የተዋቀረው የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ዋና ዳይሬክተር ዮዳዬ ዘሚካኤልም ብሔራዊ መታወቂያ ከታቀደ ብዙ ጊዜ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ በየትኛውም የአገልግሎት ዘርፍ ወሳኝ ሚና ያለውን ብሔራዊ መታወቂያ አንገብጋቢነት ያህል በቶሎ ወደ ትግበራ ሊገባ ያልቻለበት በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ይታመናል፡፡

ዜጎች ብሔራዊ መታወቂያ ማንነታቸውን የሚለይ ቁጥር እንዲኖራቸው ሳይደረግ እስካሁን መቆየቱ ግን በአገር ደረጃ እንደ ትልቅ ጉዳት እንደነበረው ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ረቂቅ ላይ እንደተገለጸውም ጠንካራ የዲጂታል የመታወቂያ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ዜጎችና ኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች የመታወቅ መብታቸው እንዳይረጋገጥ አድርጎ መቆየቱን ይገልጻል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ ዕደላ መዘግየት የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት እንዲይኖር፣ ለኅብረተሰቡ መድረስ የሚገባቸው ሕዝባዊ አገልግሎቶች ማግኘት ለማይገባቸው እንዲደርሱ ስለሚያደርግና ሕገወጥ ግለሰቦች በተለያየ ስምና ማንነት መታወቂያዎችን በመያዝ የወንጀል ድርጊቶች እንዲስፋፉ የሚያደርግ እንደሆነም ያመለክታል፡፡

በተለይ ከፋይናንስ ዘርፉ አንፃር የዚህ መታወቂያ አለመኖር ትልቅ ጉዳት ነበረው፡፡ ኢንዱስትሪው በሚታሰበው ደረጃ እንዳይራመድ ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱም ብሔራዊ መታወቂያ ሥራ ላይ ያለመዋል ነው፡፡ የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በዚህ ሐሳብ ይስማማሉ፡፡

በአጠቃላይ በብሔራዊ መታወቂያ ትግበራ ዙሪያ ማብራሪያ የሰጡት አቶ ፀሐይ፣ የብሔራዊ መታወቂያ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ይተገበራል ተብሎ የነበረው ዛሬ ያለመሆኑንና በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ በቆዩበት ጊዜያት ሁልጊዜ ሲነሳ እንደነበረ ያስታውሳሉ፡፡ በተለይም ባለፉት አሥር ዓመታት በሰፊው ሲሠራበት የነበረ ጉዳይ ነው እየተባለ እስካሁን ሥራ ላይ ለማዋል የተለያዩ እንቅፋት ሲያጋጥሙት የነበረ ቢሆንም፣ አሁንም በቶሎ ከተተገበረ በተለይ ለፋይናንስ ኢንዱስትሪው ትልቅ ትርጉም እንዳለው ያመለክታሉ፡፡

«ብሔራዊ መታወቂያ ማለት ለአንድ አገር በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው» ያሉት አቶ ፀሐይ፣ በአገሪቱ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ መሠረት በፋይናንስ ዘርፉ ተጠቃሚ ያልሆነው ብዙኃኑ ሕዝብ እንዴት አድርጎ ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ ለመመለስ ትልቁን ሚና ሊጫወት የሚችለው ብሔራዊ መታወቂያ መሆኑንም አክለዋል፡፡

«በሌሎች አገሮች ብሔራዊ መታወቂያና ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ 12 ዲጂት ያለው ቁጥር ባንኮች ማን ምን እንደሆነ ደንበኞቻቸውን በትክክል አውቀው ለደንበኞቻቸው የሚያስፈልገውን አገልግሎት እንዲሰጡ የሚረዳ ነው፤» ያሉት ሥራ አስፈጻሚው ኢትዮጵያ ውስጥ ግን የዜጎችን መረጃ የሚያሳይ ቋት ሳይኖር መቆየቱ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ተፅዕኖ እንደፈጠረ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን በነበረው ሁኔታ ማንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መረጃ አገራችንን እንደ ዋሻ የምትታይ አድርጓታል የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ በዚህ ረገድ ማን ምን እንደሆነ የማይታወቅበት ሆኖ በተለይ የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሮ እንደቆየም ሳይገልጹ አላለፉም፡፡

ይህንን መታወቂያ አዘጋጅቶ ለመስጠት ሁለት አሥርት ዓመታት የፈጀበትን ምክንያት ከፖለቲካ ሥርዓቱ ጋር የሚያያዙ ወገኖች ደግሞ፣ ወታወቂያውን መተግበር በተጭበረበረ መንገድ የተለመደን ምዝበራ የሚገታ በመሆኑ ይህንን ዕውን ከማድረግ እንደተቆጠቡ የሚገልጹ አሉ፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ አስፈላጊነትን በተመለከተ በፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ እንደሚታመነው ደግሞ፣ በኢትዮጵያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገና መሠረታዊ የሆነ ዲጂታል መታወቂያ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ልማትን ለማቀድ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪና ተጠቃሚ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር ለማድረግ፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር ሥርዓትን ለመዘርጋት የሚረዳ ነው፡፡

አቶ ዮዳዬም፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖር ዜጋም ሆነ ማንኛውም ነዋሪ ራሱን የሚለይበት ልዩ ቁጥር እንዲኖረው የማድረጉ ዕርምጃ አገራዊ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ የሙከራ ሥራ ተጀምሯል፡፡

መታወቂያው ቢዘገይም አሁን ላይ ዕውን ሊሆን እንደሚችል በተግባር እየታዩ ያሉ ክዋኔዎች አሉ፡፡ ከሰባ ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ለመድረስም ታቅዷል፡፡ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክቱ ለዜጎች መታወቂያውን ለመስጠት አራት ዓመታት ይፈጅብኛል ማለቱ ግን የተለያየ አስተያየት እየተሰጠበት ነው፡፡ ለምን ይህንን ያህል ጊዜ ይፈጃል የሚለው ጥያቄም የብዙዎች ነው፡፡

ወደ ሥራ ከገባ ገና አንድ ዓመት እንደሆነው የሚገልጹት የፕሮጀክቱ ዋና ዳይሬክተር፣ የመታወቂያውን ሥርጭት ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን የሚሠሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የብሔራዊ መታወቂያ አሰጣጡን ለመተግበር ጽሕፈት ቤቱ እየተጠቀመባቸው ካሉ መንገዶች አንዱ ደግሞ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ስምምነት በመፍጠር ብሔራዊ መታወቂያውን ዜጎች እንዲያገኙ ማድረግ ነው፡፡

ከእነዚህ ተቋማት መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት የፋይናንስ ተቋማት ሲሆኑ፣ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ እስካሁን ከአራት ባንኮች ጋር በጥምረት ለመሥራት የመግባቢያ ስምምነት አድርጓል፡፡

በሳምንቱ አጋማሽ ላይ ፕሮጀክቱ ከአዋሽ ባንክ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ያደረገ ሲሆን፣ በዚህ ስምምነት መሠረት የፕሮጀክቱ ዲጂታል አይዲ ሲስተም ከአዋሽ ባንክ ሲስተም ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ ነው፡፡ አሁን በተገባው ስምምነት መሠረት መናበብ የሚችል በመሆኑ ለብሔራዊ መታወቂያው ትግበራ ያግዛል ተብሏል፡፡

ይህ ስምምነት አንድ ደንበኛ አዋሽ ባንክ ጋር ሲመጣ መረጃው ወደ ፕሮጀክቱ ሲስተም እንዲደርስ ማድረግም ሌላው የስምምነቱ አካል መሆኑን ተገልጿል፡፡ በዚሁ ስምምነት መሠረት የባንኩ ደንበኞች ይህንን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለውን ብሔራዊ መታወቂያ እንዲያገኙና በዚያ መታወቂያ እንዲገለገሉ ለማስቻል በእንዲህ ያሉ ስምምነቶች የሚካሄደው ሥራ አሰራሩን ያቀላጥፋል ተብሎ ታምኗል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ በተለይ ከፋይናንስ ዘርፍ አንፃር ጠቀሜታን በተመለከተ አቶ ፀሐይ ጨምረው እንዳመለከቱት፣ በፋይናንስ ዘርፉ ከጎረቤት አገሮች ጭምር የተወሰደብንን ብልጫ የምናገኝበት ጥሩ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብም አቅም የሚፈጥር ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ ኬንያ በዚህ ረገድ ብዙ ርቀት መጓዟን የተናገሩት አቶ ፀሐይ፣ ሒሳብ መክፈት ሳያስፈልግ በኦላይን በሞባይል ብቻ ከባንኮች መበደር የሚቻልበትን አሠራር እንዲፈጥሩ አድርጓል፡፡

የመታወቂያው መኖር ማን ምን እንደሆነ ማረጋገጫ በመሆኑ አነስተኛ ብድር ፈላጊዎች በተለይ ደመወዝተኛ ሠራተኞች የሚያገኙትን ገቢ የሚመጥን ብድር እንዲያገኙ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በዕለቱ እንደተገለጸው፣ የብሔራዊ መታወቂያ ዕደላ መተግበር ከጀመረ ባንኮች ስምምነቶችን በማድረግ የተለየ አገልግሎት

(ወደ ገፅ 7 ዞሯል)

## የምግብ ዘይት የፋብሪካ ዋጋ መወሰኛ ሊወጣ ነው

የምግብ ዘይት የፋብሪካ ዋጋ መወሰኛ በአንድ ወር ውስጥ ተግባራዊ እንደሚያደርግ፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሚኒስቴሩ ያለቀለት የፓልም ምግብ ዘይት ለሚያስመጡና ከድፍድፍ የምግብ ዘይት ለሚያጣሩ የአገር ውስጥ ፋብሪካዎች፣ ምርቱ ከፋብሪካ ለአከፋፋዮች የሚሸጥበት ዋጋ እንደሚወሰን፣ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ዕቃዎች ዋጋ ጥናት ቡድን መሪ አቶ አሸናፊ ማሙዬ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት አልፎ አልፎ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ በሚያደርጉ ፋብሪካዎች ላይ ቁጥጥር ለማድረግ ቢሞከርም፣ ውጤታማ አለመሆኑንና ወጥ የሆነ አሠራር እንዳልነበረው ተናግረዋል።

በመሆኑም በተለይ ፋብሪካዎቹ ለድፍድፍ ዘይት ማስመጫ የሚወስዱት የውጭ ምንዛሪ ዋጋን ከማረጋጋት አንፃር የሚቀርብ ቢሆንም፣ በዋጋ ላይ ግን ጭማሪ መኖሩን ገልጸዋል። ለዚህም በአከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ላይ ከሚደረገው ቁጥጥር በተጨማሪ፣ የፋብሪካ ዋጋ መወሰን ማስፈለጉን አቶ አሸናፊ አክለዋል።

‹‹እስካሁን በሊትር ከፋብሪካ የሚወጣበት ዋጋ ባይወሰንም፣ በአንድ ወር ውስጥ ግን ተወስኖ ወደ ሥራ ይገባል፤›› ብለዋል። በአሁኑ ወቅት ገበያ ውስጥ አምስት ሊትር ፓልም ዘይት እስከ 650 ብር የሚሸጥ ሲሆን፣ ፈሳሽ የምግብ ዘይት ደግሞ ከ950 ብር በላይ እየተሸጠ ነው።

ከዋጋ መወሰኛው በተጨማሪ ፋብሪካዎች እንዲያመርቱ የሚጠበቅባቸው የዘይት መጠን እንደሚወሰን የገለጹት አቶ አሸናፊ፣ አዲስ ወደ ዘርፉ የሚገቡም ሆኑ የነባሮቹ ፋብሪካዎች ዝቅተኛ የማምረት አቅም ገደብ ይቀመጥለታል ብለዋል።

በዚህም መሠረት ፋብሪካዎቹ በቀን እስከ 200 ቶን እንዲያመርቱ ሊወሰን እንደሚችል፣ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የማሽነሪና የቴክኖሎጂ አቅም እንዲኖራቸው ያስገድዳል ሲሉ አስረድተዋል።

አምራቹ ለድፍድፍ ፓልም ግብዓት በመንግሥት የሚመደብለትን የውጭ ምንዛሪ ሙሉ በሙሉ ለተመደበለት ግብዓት ግዥ ብቻ መጠቀም እንዳለበት፣ ከድፍድፍ ፓልም ግብዓት የሚመረተው ምርት የገበያ ዋጋ ከውጭ አገር ተጣርቶ ከሚመጣው የፓልም ምግብ ዘይት ዋጋ የተሻለና ሸማቹን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን እንደሚገባው አቶ አሸናፊ ጠቁመዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ፋብሪካዎች ያመረቱትን ዘይት የሚያሠራጩበት አሠራር ግልጽነት እንዲኖረው እንደሚፈለግ፣ ትክክለኛውን የሥርጭት መንገድ ጠብቀው ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ማከፋፈል ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። በተቀመጠው መሥፈርት መሠረት የማይሠራ አምራችም ሆነ አስመጪ የአምራችነትና የአስመጪነት ፈቃዱ እንደሚሰረዝ አክለዋል።

የዋጋና የማምረት አቅም መወሰኛውን በተመለከተ ሪፖርተር ያነጋገራቸው የሸሙ የምግብ ዘይት ፋብሪካ የኮሙዩኒኬሽን ኃላፊ አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ፣ አምራቾችን የሚጎዳ ውሳኔ መሆኑን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት የሸሙ የምግብ ዘይት ፋብሪካ አንድ ሊትር የምግብ ዘይት የፋብሪካ ዋጋ 81 ብር መሆኑን ገልጸው፣ ነገር ግን የምርት ወጪው ከዚህ በፊት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየቱን አስረድተዋል። ለአብነትም ከዚህ ቀደም እስከ 700 ዶላር በቶን ይከፈልበት የነበረው ድፍድፍ ዘይት አሁን 3,000 ዶላር ደርሷል ብለዋል፡፡ በመሆኑም አምራቾች በግብዓትም ሆነ በሌሎች የምርት ወጪዎች ላይ የሚያጋጥሟቸውን የዋጋ ልዩነቶች መሠረት አድርገው ዋጋ ካላስተካከሉ በስተቀር፣ የመሸጫ ዋጋ መወሰኑ እንደሚጎዳቸው አክለዋል።

የማምረት አቅም መወሰኑም በተለይ አሁን ካለው የምግብ ዘይት እጥረትና የዋጋ ከፍ ማለት አንፃር ትክክለኛ ዕርምጃ እንደማይሆን ተናግረዋል። አዳዲስ ወደ ዘርፉ የሚመጡትንም የማያበረታታ ነው ብለዋል፡፡ የግብዓት እጥረት ፈታኝ በመሆኑ አሁን ያሉት ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንደማያመርቱ የገለጹት አቶ ቴዎድሮስ፣ ሸሙ የምግብ ዘይት ፋብሪካ በቀን 1,187 ቶን የማምረት አቅም ቢኖረውም ከ30 በመቶ በታች አቅሙን እየተጠቀመ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25111

## በኦጋዴን የተፈጥሮ ነዳጅ የሚያጠና የአሜሪካ ኩባንያ ሥራ ሊጀምር ነው

በኢትዮጵያ ደቡብ ምሥራቅ ክፍል በኦጋዴን ቤዚን በጥናትና በቁፋሮ የተገኘውን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ለኢንቨስትመንት ጥቅም ለማዋል የሚያግዝ የማማከርና የጥናት ሥራ ለማከናወን የተስማማው፣ የአሜሪካ ኔዘርላንድ ስዌል ኤንድ አሶሼትስ ኢንክ ኩባንያ ከቀጣዩ ሳምንት ጀምሮ ሥራ ሊጀምር ነው፡፡

ኩባንያው የሚያካሂደው ጥናት ውጤት በኦጋዴን የሚገኘውን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ለማዳበሪያና ለኢነርጂ ኢንቨስትመንቶች ጥቅም ላይ እንዲውል፣ እንዲሁም ከጋዝ ወደ ፈሳሽ ነዳጅ ለመቀየር ተብሏል፡፡

የማማከርና የጥናት ሥራውን ለማከናወን ዓለም አቀፍ ጨረታ ወጥቶ የኔዘርላንድ ስዌል ኤንድ አሶሼትስ ኢንክ ኩባንያ አሸናፊ መሆኑን የማዕድን ሚኒስቴር አስታውቋል፡፡ ኩባንያው በሶማሌ ክልል ኦጋዴን ቤዚን 3,500 ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ላይ የተከናወኑ የፍለጋና የጥናት ውጤቶችን መነሻ በማድረግ፣ በቤዚኑ ያለውን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት መጠን የሚያሳውቅና ኢኮኖሚያዊ ግምገማ የሚያሳይ ጥናት የሚያከናውን እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

ማክሰኞ መጋቢት 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር ስምምነት ያደረገው ኩባንያው፣ በዘርፉ ያሉት ባለሙያዎችና በበርካታ አገሮች ያከናወናቸውን ሥራዎች ከግንዛቤ ተወስደው፣ የማዕድን ሚኒስቴር እንደመረጠው ገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብቶች እንዳሉ በጥናትና በቁፋሮ የተረጋገጠ እንደሆነ ያስታወቀው የማዕድን ሚኒስቴር፣ ሀብቱን ወደ ኢንቨስትመንት ደረጃ ለማሳደግ የተለያዩ ተግዳሮቶች ሲያጋጥሙ መቆየታቸውን አክሏል፡፡

የኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ማረጋገጫ እንዲኖረው ማድረግ ሌላው በኩባንያው የሚከናወን የጥናት ዓላማ እንደሆነ በስምምነት ፊርማው ወቅት የተገለጸ ሲሆን፣ ይህ ዓለም አቀፍ ማረጋገጫ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብቱን እንደ አገር ሀብት የሚያስቆጥረው በመሆኑ ኢትዮጵያ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ለሚኖራት ተሳትፎ እንደ መንደራደሪያነት የሚጠቅማት ይሆናል ተብሏል፡፡

የኔዘርላንድ ስዌል ኤንድ አሶሼትስ ኢንክ ኩባንያ ምክትል ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ዎልፍ ለሪፖርተር እንዳስታወቁት፣ የአማካሪ ኩባንያው በዓለም አቀፍና በአፍሪካ ደረጃ አገሮች ያላቸውን የማዕድን ሀብት መጠን የተመለከተ ጥናቶችን ያከናውናል፡፡ ይህም አገሮች ያላቸውን የማዕድን ሀብት መጠን መሠረት አድርገው እንዴት ለራሳቸውና በውጭ ገበያ ለገቢ ማግኛ ምንጭነት ሊጠቀሙባት የሚያስላቸው እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ኩባንያው ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር የተፈራረመው ስምምነት በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ የኦጋዴን ቤዚን የሚገኘውን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት በምን ያህል መጠን እንደሚገኝ፣ ይህንንም ማዕድን ሚኒስቴር በሚያስቀምጠው አሠራር መሠረት ሌሎች በነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ማውጣት ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ሊጠቀሙበት በሚቻልበት መንገድ መረጃ ለመተንተን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ኩባንያው ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጋር የተፈራረመው ስምምነት የአራት ወራት የጊዜ ገደብ ያለው እንደሆነ የተናገሩት ሚስተር ዎልፍ፣ ድርጅቱ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ ወደ ትግበራ የሚሸጋገር እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በተጠቀሱት ወራት ውስጥ  የተጠናቀረ መረጃ በሪፖርት መልክ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚቀርብ መሆኑን፣ ይህም ተቋሙ በቀጣይ ለሚያደርገው ሥራ የሚጠቅመው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ኩባንያው የሚጠቀመው መረጃ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በኩል የተዘጋጀ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፣ ከዚያ ውጪ አዲስ መረጃ ማዘጋጀት እንደማይጠበቅበት ተገልጿል፡፡ አገሪቱ ከነዳጅ ሀብቷ ጋር የተገናኙ በርካታ የሴስሚክና የሰብኮር መረጃዎች ስላሏት፣ ይህንን መረጃ በመጠቀም ምን ያህል የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብቱ መጠን ይገኛል? ምን ያህልስ ማምረት ይቻላል? የሚለው የሚወሰን እንደሆነ ምክትል ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል፡፡

የመጀመሪያውን የስምምነት ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ወዲያውኑ ቀጣይ ስምምነት የማድረግ ዕቅድ በዚህ ወቅተ ይደረጋል ተብሎ መገመት እንደማይቻል ያስታወቁት ሚስተር ዎልፍ፣ ከኮንትራቱ መጠናቀቅ በኋላ የሚከናወኑ ጉዳዮች ካሉ በሁለቱ አካላት የጋራ ስምምነት መሠረት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

በስምምነት ሥነ ሥርዓቱ ላይ የማዕድን ሚኒስትሩ ታከለ ኡማ (ኢንጂነር)፣ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ትሬሲ ጃኮብሰን፣ እንዲሁም የኩባንያው ተወካዮችና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

የማዕድን ሚኒስቴር በጥናትና ቁፋሮ የተገኙ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሀብት ውጤቶችን ለማልማት፣ ለማሳደግና በኢንቨስትመንት ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ እንደሚገኝ የማዕድን ሚኒስትሩ ተናግረዋል፡፡

በሰኔ ወር 2013 ዓ.ም. የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር በሶማሌ ክልል የተገኘውን የተፈጥሮ ጋዝ አልምቶ ኤክስፖርት ለማድረግና ለተጨማሪ የፔትሮሊየም (የነዳጅ ዘይት) ፍለጋና ልማት፣ በዚሁ አካባቢ ለማካሄድ ፈቃድ ላገኘው የቻይና ፖሊጂሲኤል ኩባንያ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ይታወሳል።

የቻይና ኩባንያው በሶማሌ ክልል ካሉብና ኢላላ የተገኘውን ከፍተኛ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት አልምቶ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ፈቃድ ያገኘው እ.ኤ.አ. በ2013 ቢሆንም፣ በአካባቢው የሚገኘውን የተፈጥሮ ጋዝ አልምቶ ለገበያ ለማቅረብ እያደረገ ያለው ጥረት እጅግ ደካማ ከመሆኑም በላይ፣ ለመንግሥት ባቀረበው መርሐ ግብር መሠረት እያከናወነ አለመሆኑን በመጥቀስ ሕጋዊ ዕርምጃ ከመውሰዱ በፊት የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንደሰጠው መዘገቡ አይዘነጋም፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.ethiopianreporter.com/article/25026

## የባንኮች ብድር አሰጣጥን …(ከገፅ 6 የዞረ)

ይዘው እንዲቀርቡ ጭምር የሚያደርግ ይሆናል፡፡ ባንካቸው በዚህ ረገድ ሰፊ ዝግጅት ማድረጉን የጠቀሱት አቶ ፀሐይ፣ ብሔራዊ መታወቂያ የያዘ ሰው መታወቂያውን ባገኘ በማግስቱ በአዋሽ ባንክ ሒሳብ ሳይከፍት ኦላይን ብድር መውሰድ የሚችልበት ዕድል ይሰጣል፡፡

ብድሩን የሚወስደው ሰው ማን ምን እንደሆነ የሚታወቅ በመሆኑ እንደ ከዚህ ቀደሙ የደንበኛውን ማንነት በመለየት ጊዜ የማይጠፋ፣ ማስያዥ አምጣ ተብሎ ግዳጅ ውስጥም አይገባም፡፡

እስካሁን ባለው የኢትዮጵያ የባንክ አገልገሎት ውስጥ ባንኮች ከሚፈለገው በላይ ዋስትና ላይ ያተኮረ ብድር እንዲሰጡ ያደረጋቸው ይኸው የብሔራዊ መታወቂያ ያለመኖር መሆኑን የተለያዩ ምሳሌዎችን በመጥቀስ አቶ ፀሐይ ያብራሩ ሲሆን፣ ያገኙ መታወቂያው ብዙዎች የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል፡፡

ከብድር አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ደረጃ ከሚሰጠው ብድር ከ85 በመቶ በላይ ከተሞች ላይ ብቻ እንዲወሰን ካደረጉ ምክንያቶች መካከል በዋናነት ሊጠቀስ የሚችለው ይኸው የብሔራዊ መታወቂያ ያለመኖር መሆኑም ተገልጿል፡፡

በሌላው ዓለም ብዙውን ጊዜ ሰዎች ንብረት አስይዘው የማይበደሩት ሌላ ምክንያት ኖሮ ሳይሆን ብሔራዊ መታወቂያ ስላላቸው መሆኑን የጠቀሱት አቶ ፀሐይ፣ ብድር የሚወስዱት በማንነታቸው ነው ይላሉ፡፡  ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ብሔራዊ መታወቂያ ባለመኖሩ ሳይፈልጉ ንብረታቸውን እንዲያስይዙ ወይም ሕንፃ ያላቸው ሰዎች ብቻ ተጠቃሚ ያደረገበት ሁኔታ ፈጥሮ ቆይቷል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ ጉዳይ ለፋይናንስ ዘርፍ በተለይ ጠቀሜታ አለው ሲባል ለባንክ ለተገልጋዮችም የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም ንብረት በመያዝ የተመሠረተውን የኢትዮጵያን የብድር አሰጣጥ በመቀየርና ውስን ሆኖ የቆየውን የተበዳሪዎች ቁጥር ትርጉም ባለው መልኩ ከፍ በማድረግ ረገድ የዚህ መታወቂያ ዕውን መሆን ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ ጠቀሜታ በዚህ ብቻ የማይገለጽ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ፀሐይ፣ ከባንክ ሥራ ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ማጭበርበሮችን በማስቀረት ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ መሆኑንም ያነሳሉ፡፡ አቶ ዮዳዬም፣ በባንክ አካባቢ ያለን የመጭበርበርና የወንጀል ሥራን በማስቀረት ይጠቅማል ብለው ለምሳሌ የጠቀሱት ከቼክ ማጭበርበር ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር ማስቻሉን ነው፡፡

ከፋይናንስ ተቋማት አንፃር ደንበኞችን በደንብ መለየት የግድ በመሆኑ ይህንን በመለየት ረገድ የሚጠፋን ጊዜ ማቃለልና አንድ የሚመነዘርን ቼክ ትክክለኛው ሰው ለመስጠት ያስችላል፡፡

‹‹99 በመቶው የሚሆነው አያጭበረብርም የሚያጭበረብረው ትንሽ ነው፤›› ያሉት አቶ ዮዳዬ፣ ነገር ግን አጭበርባሪዎቹ በሚፈጥሩት ችግር ሌሎቹም ይጎዱ ስለነበር የመታወቂያው ዕውን መሆን እንዲህ ያሉ ወንጀለኞችንም ለመከላከል የሚያስችል መሆኑን ከሰጡት ማብራሪያ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

አዋሽ ባንክ ከሰባት ሚሊዮን በላይ ደንበኞች እንዳሉት የገለጹት አቶ ፀሐይ፣ እነዚህ ደንበኞች ይህንን መታወቂያ እንዴት ሊያገኙ ይችላሉ በሚለው ላይ ከፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ ጋር ሆኖ በመሥራት ለተገልጋዮች አዳዲስ አገልግሎት የሚቀርብ መሆኑንም በማስታወቅ አሁን የተጀመረው ሥራ ለባንክ ኢንዱስትሪው እንደ ትልቅ ዕድል የሚታይ ነው ብለዋል፡፡

መታወቂያው አነስተኛ ተበዳሪዎች ብድር እንዲያገኙ ከማስቻሉም በላይ ዜጎች ሕይወታቸውን በፕሮግራም እንዲመሩ የሚያግዝ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አንድ ብሔራዊ መታወቂያ የያዘ ዜጋ በየትኛውም ቦታ አገልግሎት የሚያገኘው በዚህ መታወቂያው ነው፡፡

በዚህ መታወቂያ የሚሰጠው አገልግሎት ወይም ያገኘው አገልግሎት በየትም ቦታ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ አንድ ተበዳሪ ብድር ካልከፈለ በየትም ቦታ ተጨማሪ ተመሳሳይ አገልግሎት አያገኝም፡፡ ስለዚህ በጥንቃቄ ተጠቅሞ ብድርን መክፈል ግድ ይለዋል፡፡ ከከፈለ ተጨማሪ ብድር እየተሰጠው የሚፈልገውን ማድረግ የሚችል በመሆኑ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ለመፍጠርም አጋዥ ይሆናል ተብሏል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያው ልዩ ቁጥር የባንክ፣  የጤና፣ የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኝ ራሱን በልዩ ሁኔታ እንዲለይ ይጠቅማል፡፡ ይህ ልዩ ቁጥር ከነዋሪ መታወቂያ፣ ከመንጃ ፈቃድ፣ ከባንክ፣ ከኢንሹራንስና ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር ሊተሳሰር የሚችል መሆኑን የገለጹት አቶ ዮዳዬም፣ እከሌ በትክክል እከሌ ነው ብሎ ማረጋገጥ ያስችላል ይላሉ፡፡

በዋናነት ግን በኢትዮጵያ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገና መሠረታዊ የሆነ ዲጂታል መታወቂያ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ልማትን ለማቀድ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አገልግሎት ሰጪና ተጠቃሚ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር ለማስቻል፣ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሠራር ሥርዓትን ለመዘርጋት ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25067

## ከጂኦተርማል የኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ የሚያስችል የግንባታ ምዕራፍ ሊጀመር ነው

በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን ኢተያ ወረዳ 150 ሜጋ ዋት የጂኦርተርማል ኃይል ለማመንጨት ቁፋሮው የተጀመረው የቱሉ ሞዬ ጂኦርተርማል ኩባንያ፣ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሚያቀርብበትን የግንባታ ምዕራፍ ሊጀምር ነው፡፡

ኩባንያው ይህንን የኃይል ምንጭ ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለማቅረብ የሚደረገውን የኢንጂነሪንግ፣ የግዥና የግንባታ ስምምነት ዓለም አቀፍ ጨረታን መሠረት በማድረግ በጥምረት አሸናፊ ከሆኑት የጃፓኑ ሚትስቡሺ ኮርፖሬሽን፣ እንዲሁም የቻይናው ሴፒኮ ሦስት የአሌክትሪክ ኃይል ኮንስትራክሽን ኩባንያ ጋር ባለፈው ሳምንት ተፈራርሟል፡፡

ከኩባንያዎቹ ጋር የተደረገው ስምምነት ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፣ ይህንን የገንዘብ ፈሰስ የፈረንሣይ ኢንቨስትመንት ፈንድ አቅራቢ የሆነው ሜሪዲየም፣ እንዲሁም የአይስላንድ ጂኦተርማል ድርጅት የሆነው ሬዩጃቪክ ይሸፍኑታል ተብሏል፡፡

የቱሉ ሞዬ ጂኦተርማል ቺፍ ቴክኒካል ኦፊሰር አቶ የትምጌታ ፋንቱ ለሪፖርተር እንዳስታወቁት፣ ሁለቱ ኩባንያዎች አሸናፊ የሆኑበት የፍላጎት ማሳወቂያ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው በሚያዚያ 2011 ዓ.ም. ነበር፡፡

በፕሮጀክቱ የቅድመ ምዘና ሒደት ላይ እንዲሳተፉ 22 ድርጅቶች መጋበዛቸውን፣ ከዚህ ውስጥ ሰባቱ ድርጅቶች ተመዝነው መመረጣቸውንና የዋና ጨረታ ሰነድ የተላከላቸው መሆኑን፣ ከእነሱ ውስጥ አምስቱ የጨረታ ተሳታፊነት ሰነድ መልስ እንዳስገቡ ታውቋል፡፡ በመጨረሻም የሁለቱ ድርጅቶች ጥምረት ሊመረጥ እንደበቃ ተገልጿል፡፡

አሸናፊ የሆኑት ድርጅቶች ለጂኦተርማል ኃይል ከተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የኃይል ማስተላለፊያ ቱቦ (ፓይፕ) ዘርግተው ወደ ኃይል ማመንጫ አካባቢ እንደሚያመጡ ያስረዱት አቶ የትምጌታ፣ የዋና ኃይል ማመንጫ ግንባታውንና ለኃይል ማመንጫነት የሚረዳውን 50 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያለውን ተርባይን፣ እንዲሁም ጄኔሬተር ከግዥ አንስቶ እስከ ተከላ ያለውን ሥራ እንደሚያከናውኑ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል የጂኦተርማሉ ኃይል ከመነጨ በኋላ ከብሔራዊ የኃይል ቋት ጋር የሚገናኝበትን ሰብስቴሽን የሚሠሩት ድርጅቶቹ፣ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ከጂኦተርማል የሚገኘውን የኤሌክትሪክ ኃይል እ.ኤ.አ በኅዳር 2024 ለማመንጨት የቀነ ገደብ እንደተቀመጠላቸው አቶ የትምጌታ አስረድተዋል፡፡

‹‹ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ያለን ሰምምነት በመጀመሪያ የሚመነጨውን የ50 ሜጋ ዋት ኃይል ተቀብለው ወደ ዋና የኃይል መስመር እንደገባ ነው፤›› ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የቱሉ ሞዬ ጂኦርተርማል ሚና የሚመነጨውን ኃይል ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል ቋት ማስተላለፍ ብቻ እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ከኢትዮጵያ አሌክትሪክ ኃይል ጋር የሚደረገው የኃይል ሽያጭ ግብይት የሚመነጨውን ኃይል መሠረት ያደረገ እንደሆነ ያስረዱት አቶ የትምጌታ፣ በሰዓት 50 ሜጋ ዋት የሚመነጭ ከሆነ ይህ በ24 ሰዓታትና በ365 ቀናት ተባዝቶ የሚታሰብ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ከውኃ ከሚመነጨው የኃይል አማራጭ ጀምሮ ከንፋስም ሆነ ከፀሐይ ብርሃን የሚገኙ የኃይል አቅርቦቶች ከእንፋሎት (ጂኦተርማል) ጋር ሲነፃፀሩ ከተፈጥሯዊ ባህሪያቸው አንፃር የሚያመነጩት የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን ከፍና ዝቅ እንደሚል የተነገረ ሲሆን፣ ነገር ግን ጂኦተርማል አረንጓዴነት የተላበሰና አትራፊ ወይም ገበያ ሊገኝለት የሚችል አማራጭ እንደሆነ ተመላክቷል፡፡

የተለያዩ አገሮች ፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች የፕሮጀክቱን ውጤታማነት ወይም ተስፋ ሰጪነት ተመልክተው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ማለት ኢንቨስት የሚያደርጉበት ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው ያሉት አቶ የትምጌታ፣ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ የግል ዘርፎች ላይ ድጋፍ ማድረጋቸው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱን የሚያሳድግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በመጀመሪያው ምዕራፍ ብቻ 270 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስት የሚደረግበት እንደሆነ ያስረዱት ዳይሬክተሩ፣ ይህም ለመንግሥትም ሆነ ሌሎች ኢንቨስተሮች ጥቅሙ የጎላ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ቱሉ ሞዬ ከመንግሥት ጋር ያለው ኮንትራት በሁለት መዕራፎች የሚያደርጋቸው የኃይል ሽያጭ ስምምነቶች ሲሆኑ፣ የሁለቱንም ደረጃዎች የጊዜ ፍሰት ተከትሎ እየሠራ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

በተለይም ይህ የኃይል አማራጭ ታዳሽ፣ ከመሬት ወጥቶ መልሶ የሚጠቅም በመሆኑ በተለይም ወጥነት ያለው የኃይል አማራጭ ለሚፈልጉ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመሳሰሉ ተቋማት አስፈላጊ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡

‹‹አንድ የኃይል ማመንጫ አማራጭ ላይ ጥገኛ ሆኖ መቆየት አይቻልም፤›› ያሉት አቶ የትምጌታ፣ በመሆኑም በአንድ አገር ላይ የተለየ የኃይል አማራጮችን መጠቀም አስፈላጊነቱን ጠቅሰዋል፡፡

ከሚታደሱ የተፈጥሮ የኃይል ምንጮች መካከል የጂኦተርማል ኃይል አንዱ ሲሆን፣ ይህ ኃይል ከከርሰ ምድር የሚወጣውን የጭስ ሙቀት ወደ ጉልበት እንዲቀየር በማድረግ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

በኢትዮጵያ የአሉቶ ላንጋኖ ጂኦተርማል ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት በተጠቀሰው የኃይል አማራጭነት ለመጠቀም ጥረት የተደረገበት ነገር ግን ተጀምሮ የቆየ ሲሆን፣ ቱሉ ሞዬ ይህንን ኃይል በአማራጭነት ለመጠቀም እየተቃረበ እንደሆነ ይነገራል፡፡

በኬንያው የቁፋሮ ድርጀት ኬንጂን የሚከናወነው ቁፋሮ በዚህ ወቅት አራተኛው ቁፋሮ ላይ እንደደረሰ ታውቋል፡፡

በመጀመሪያው የፕሮጀክቱ ምዕራፍ 50 ሜጋ ዋት ኃይል የሚመነጭ መሆኑን፣ በሁለተኛው የፕሮጀክቱ ምዕራፍ ደግሞ 100 ሜጋ ዋት ኃይል በድምሩ እ.ኤ.አ 2025 ድረስ 150 ሜጋ ዋት ኃይል ይመነጫል ተብሎ ይጠበቃል ተብሏል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25119

## በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾችን ሥጋት ላይ የጣለው የውጭ ምንዛሪ ዕጦት

ወቅታዊው የውጭ ምንዛሪ እጥረት አሳሳቢ ስለመሆኑ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እየተሰሙ ያሉ ድምፆች እያመላከቱ ነው፡፡ በተግባርም የውጭ ምንዛሪ እጥረት ጥቂት የማይባሉ አምራች ኢንዱስትሪዎችን ሳይቀር ከአቅም በታች እንዲያመርቱ እያስገደደ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራት ኮንፌዴሬሽንም ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በተያያዘ በምርትና ምርታማነት ላይ እየተስተዋለ ያለው ችግር እንዳሳሰበው ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡ ይህ በብዙዎቹ የንግድና አምራች ዘርፎች ላይ እየታየ ያለው የውጭ ምንዛሬ ዕጦት ችግር፣ በተለይ ከውጭ የሚገባ ጥሬ ዕቃን በዋናነት የሚጠቀሙ የተለያዩ አምራቾችን በእጅጉ እየተፈተነ ነው። የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ በዚሁ ከቀጠለ ሥራ ወደ ማቆም ደረጃ እንደርሳለን፣ ሠራተኛም እንበትናለን እስከ ማለት የደረሱ መኖራቸውም እየተሰማ ነው።

ለጥሬ ዕቃ የሚሆን የውጭ ምንዛሪ በማጣት ከአቅማቸው በታች እያመረቱ ካሚገኙ አምራች ዘርፎች ውስጥ የፕላስቲክ፣ ጎማና ተያያዥ የሆኑ ምርቶችን የሚያምርቱ ተጠቃሽ ናቸው።

የኢትዮጵያ ፕላስቲክና ጎማ አምራቾች ማኅበር ባለፈው ቅዳሜ መጋቢት 17 ቀን 2014 ዓ.ም. 2014 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው የፕላስቲክና ተያያዥ ምርቶችን የሚያመርቱ አምራቾች በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ችግር ውስጥ መግባታቸውን አስታውቋል፡፡

ይህ ዘርፍ በግብዓትነት ለሚጠቀመው ጥሬ ዕቃ መግዣ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት አለመቻሉ እያስከተለ ካለው ጉዳት በተጨማሪ፣ ዘርፉ እጅግ ሰፊና ከሌሎች አምራቾች ጋር የጎንዮሽ የንግድ ትስስር ያለው ከመሆኑ አኳያ በዚህ ዘርፍ ላይ የሚፈጠር እክል ሌሎች የንግድ ዘርፎችንም እንደሚያስተጓጉል ማኅበሩ ሥጋቱን ገልጿል። በዚህም ምክንያት አገራዊ ኢኮኖሚው ላይ ብርቱ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ እንደሚችል አሳስቧል።

በማኅበሩ ሥር ከ4,5000 በላይ የፕላስቲክና ጎማ አምራቾች መኖራቸውንና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠሩ አምራቾች እንደሆኑ የማኅበሩ መረዎች ያመለክታሉ።

ዘርፉ በ100 ቢሊዮን ብር የሚገመት ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት እንደሆነ ያመለከቱት የማኅበሩ አመራሮች፣ ከውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ጋር በተያያዘ የገጠመው ችግር ካልተፈታ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ ሊፈጥር ይችላል የሚል ሥጋት እንዳሳደረባቸው ገልጸዋል።

ማኅበሩ በቅርቡ አደረኩት በሚለው የዳሰሳ ጥናት ከ85 በመቶ በላይ የሚሆኑት ፋብሪካዎች ከአቅማቸው ከግማሽ በታች እያመረቱ እንደሆነ ያስታወቀ ሲሆን፣ የዚህም መሠረታዊ ምክንያቱ ይኼው የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደሆነ የኢትዮጵያ የፕላስቲክና የጎማ አምራቾች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ ምንተስኖት ለማ ገልጸዋል፡፡ ‹ይህ እንደ አገር በጣም ከፍተኛ ጉዳት የሚያመጣ ስለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል፤›› ያሉት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት፣ በተለይ አሁን ላይ ችግሩ እየተባባሰ ስለመምጣቱ ይገልጻሉ። ለዚህ ችግር ዋነኛ ምክንያት ደግሞ እነዚህ የፕላስቲክ ማምረቻዎች በግብዓትነት የሚጠቀሙባቸው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለማስገባት የሚያስችል የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የተደረጉ ጥረቶች ሁሉ ሊሳኩ አለመቻላቸው እንደሆነ የገልጻሉ።

በመሆኑም ለእነዚህ ማምረቻዎች በቀጥታ የውጭ ምንዛሪ እንዲያገኙ መንግሥት ሁኔታዎችን ካላመቻቸ ብዙዎቹ ፋብሪካዎች ተዘግተው ሠራተኞች ሊበተኑ እንደሚችሉ ሥጋታቸውን ገልጸዋል፡፡

ከሰሞኑ ዘርፉ ያለበትን ችግር በተመለከተ ከገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ጋር መነጋገራቸውን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፣ ሚኒስትሩ ጥሩ ምላሽ እንደሰጧቸውና ችግሩ በሒደት እንደሚፈታ እንደገለጹላቸው ተናግረዋል፡፡ ‹ሆኖም አሁን ካለው ችግር አንፃር እስከ መቼ የሚለው ጥያቄ መልስ አላገኘም፡፡ ስለዚህ በትንሹ ችግሩን ለመፍታት እንዲረዳ የውጭ ምንዛሪ ለፋብሪካዎቻችን ሊፈቀድልን ይገባል፤›› ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፣ ለእነዚህ ፋብሪካዎች የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን በአስመጪዎች በኩል እንዲመጡና ገበያ ላይ እንዲሸጡ ከመፍቀድ፣ በቀጥታ ፋብሪካዎቹ እንዲያስመጡ የሚያስችላቸውን የውጭ ምንዛሪ ቢፈቀድላቸው ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡ ለዋጋ መረጋጋትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው የሚል እምነት አላቸው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አጠቃቀምን በተመለከተ በቅርቡ በወጣው መመርያ ኢንዱስትሪዎችና አምራቾች ቅድሚያ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያገኙ ቢደነግግም፣ የፕላስቲክ ዘርፉ ግን በዚህ መመርያ መሠረት ተጠቃሚ እንዳልሆነም ማኅበሩ አስታውቋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ የተጠየቁት የማኅበሩ ፕሬዝዳንት አቶ ምንተስኖት፣ ‹‹በመመርያው መሠረት ከመድኃኒትና ከሕፃናት ምግብ ቀጥሎ ቅድሚያ የሚሰጣቸው የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን አሁን ካለው ወቅታዊ እጥረት አንፃር ለመድኃኒቱም፣ ለሕፃናት ምግብም የውጭ ምንዛሪው እየቀረበ አይደለም፤›› ብለዋል፡፡

በማከልም ማኅበሩ ባደረገው ጥረት የግል ባንኮች በሚቻሉት መጠን ዘርፉን እንዲደግፉ በማድረግ በምትገኘ መጠነኛ የውጭ ምንዛሪ ብቻ የዘርፉ አምራቾች ለመንቀራቀስ እየሞከሩ ቢሆንም ችግሩ የከፋ ነው ብለዋል፡፡

‹‹የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይህንን መመርያ ሲያወጣ በጣም ደስተኛ ነበርን፤›› ያሉት አቶ ምንተስኖት፣ ከሚገኘው አገራዊ የውጭ ምንዛሪ ውስጥ 70 በሙቶን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በማስቀረት ለፋብሪካዎች፣ ለመድኃኒትና ለሕፃናት ምግብ አስመጪዎች ቅድሚያ ሰጥቶ በንግድ ባንክ በኩል በአግባቡ ያከፋፍላል የሚል ግምት እንደነበራቸው፣ ነገር ግን ይህ ባለመሆኑ የፕላስቲክና ጎማ አምራች ዘርፍ ትልቅ ፈተና እንደተደቀነበት ገልጸዋል፡፡

ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ ከወጣ ጀምሮ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል ምንም ዓይነት የተገኘ የውጭ ምንዛሪ ያላገኙ መሆኑን ያስታወሱት ፕሬዚዳንቱ፣ መመርያው በአግባቡ ተተግብሮ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የውጭ ምንዛሪው ቢለቀቅ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መረጋጋት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክት ነበር ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ድረስ የውጭ ምንዛሪ ሊያቀርብ የሚችል በመሆኑ የአምራቹን ጥያቄ በመመለስ ኢኮኖሚው ላይ ሊፈጠር የሚችለውን ጫና ያቃል እንደነበር የሚገልጹት ፕሬዚዳንቱ፣ በአዲሱ መመርያ ምክንያት ግን ንግድ ባንክ 70 በመቶ የሚሆነውን ለብሔራዊ ባንክ ማስረከብ ስለሚገደድ ይህንን ማድረግ በቂ የውጭ ምንዛሪ ማቅረብ እንደማይችል አስረድተዋል።

መንግሥት የገጠመውን ችግር እንደሚገነዘቡና ከዚህም አኳያ ሰፊ የውጭ ምንዛሪ ከመንግሥት እንደማይጠብቁ የሚገልጹት ፕሬዝዳንቱ፣ ቢያንስ ከ200 እስከ 300 ሚሊዮን ዶላር እንኳን ቢገኝ ወሳኝ የሚባሉ ምርቶችን ለማምረት የሚያስችሉ ጥሬ ዕቃዎችን በማስገባት በዘርፉ የሚንቀሳቀሱ ኩባንያዎችን ማዳን እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

ይህ ባለመሆኑ የፕላስቲክ አምራቾችን ምርት የሚጠብቁ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች በምርት እጥረቱ ሳቢያ ችግር ውስጥ መግባታቸውን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም እንደ ማሳያ ከማኅበሩ መሪዎች የተነሳው በአሁኑ ወቅት በታሸገ ውኃ ላይ እየታየ ያለው የዋጋ ጭማሪና ወደ 20 የሚሆኑ የውኃ አምራቾች ምርት ሊያቋርጡ መገደዳቸውን የማኅበሩ አመራሮች ጠቅሰዋል።

ፕላስቲክ አምራቾች ሙሉ በሙሉ ጥሬ ዕቃዎችን ከውጭ የሚያስመጡ መሆኑን የጠቀሱት የማኅበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሳምሶም ከተማ በበኩላቸው፣ የውጭ

(ወደ ገፅ 9 የዞረ)

# በሺዎች የሚቆጠሩ አምራቾችን ...(ከገፅ 8 የዞረ)

ምንዛሪ ችግሩ ተፈትቶ ጥሬ ዕቃ ማስገባት ካልተቻለ ውሃ አምራቾች እንደገጠማቸው ችግር ምርቶችን ለማሸግ የፕላስቲክ ምርቶችን የሚጠቀሙ ድርጅቶችም ችግር ውስጥ መግባታቸው እንደማይቀር ገልጸዋል ፡፡

ጥሬ ዕቃው ነዳጅን መሠረት ያደረገ ምርት በመሆኑ፣ በአገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ሊሸፈን የማይችል፣ የግድ ከውጭ የሚገኝ ምርትን የሚጠበቅ በመሆኑ፣ መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ ለዘርፉ ማድረግ እንዳለበት አመልክተዋል፡፡ ከ20 በላይ የውኃ ፋብሪካዎች የተዘጉት በአብዛኛው ከውጭ ምንዛሪ እጥረት ጋር በተያያዘ እንደሆነ የገለጹት አቶ ምንተስኖት፣ «ሰሞኑን የታሸገ የውኃ እጥረት የተከሰተውም በፕላስቲክ እጥረት ነው፡፡ የፕላስቲክ ኢንዱስትሪ ግብዓት ማግኘት አለበት፡፡ ለሌሎችም ኢንዱስትሪዎች የሚገለገሉበትና እንደ ጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙበትን ምርት የምንሰጠው እኛ ጥሬ ዕቃ አግኝተን ማምረት ስንችል ነው፤» ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ አክለው እንደተናገሩት የፕላስቲክና ጎማ አምራቾች ሲቆሙ ሌሎችም አብረው ይቆማሉ ብለዋል፡፡

«የውኃ ፋብሪካዎችም እኛ የፕላስቲክ ኮዳውን አምርተን ካላቀረብንላቸው መሥራት አይችሉም። ስለዚህ የውኃ መወደድ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ከገበያ መጥፋትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንዲያውም የሚያሠጋው ይህ ነው፤» በማለት ያለውን ችግር አስረድተዋል፡፡

አሁን ላይ ማምረት ከሚችሉት ከ10 እስከ 20 በመቶ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ጭምር እንዳሉ በመጥቀስም፣ ይህ እንደ አገር ከፍተኛ ጉዳት ስለሆነ ለፕላስቲክ አምራቾች ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የግል ዘርፉ በውጭ ምንዛሪ እጥረት እንዳይስተጓጎል ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ብለዋል፡፡ በአሥርና በሃያ በመቶ አቅም እየተመረተ ፋብሪካ ሊቆይ እንደማይችል የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፣ በዚህ መንገድ ሠራተኞቹን አንድና ሁለት ዓመት ይዞ ሊቆይ የሚችለው ጠንካራ ፋብሪካ ብቻ እንደሆነ አስረድተዋል።

በመሆኑም ትኩረት ሰጥቶ መፍትሔ ሊፈለግ እንደሚባ አመልክተዋል፡፡ ውጭ የሚላኩ የኢትዮጵያ የወጪ ንግድ ምርቶች በአብዛኛው «ፒፒ» በሚባለው ማዳበሪያ ታሽጎ የሚላክ በመሆኑና የማዳበሪያ ከረጢቱ ደግሞ የሚመረተው ከፕላስቲክ በመሆኑ ችግሩ የኤክስፖርት ዘርፉን ጭምር መንካቱ እንደማይቀር ጠቁመዋል።

ለዚህ የሚሆን ጥሬ ዕቃ ካልቀረበ ይህ ምርት ራሱ እጥረት ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ሥጋታቸውን ያነሱት የማኅበሩ አመራሮች፣ ገበሬውም እህል የሚሰበስበው፣ የሚያዘጋጀውና የሚያከማቸው በፒፒ ከረጢት በመሆኑ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግሩ ካልተፈታ የሚከሰተው ጉዳት በአንድ የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ብቻ የሚወሰን እንደማይሆን ገልጸዋል፡፡

«አሁን ትልቁ ሥጋታችን የእኛ አምራቾች አለማምረታቸው ብቻ ሳይሆን የሚጎዳው የቢዝነስ ዘርፍ ብዙ መሆኑ ያሳስበናል፤» ብለዋል፡፡

የፕላስቲክ ፋብሪካዎች በዓለም ላይ ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረ 70 እና 80 ዓመታት ብቻ ዕድሜ ያለው ቢሆንም፣ በፍጥነት እያደገ ትልቅ ኢንዱስትሪ ሆኗል፡፡ ኢትዮጵያም በእነዚህ ምርቶች ላይ በእጅጉ ተቆራኝታለች፡፡ በዓለም በፕላስቲክ የመጠቀሙ ልምድ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣና እያደገ የሚገኝ በመሆኑ ቀድሞ ከብረት፣ ከእንጨት፣ ከጥጥና ከተለያዩ ግብዓቶች ይሠሩ የነበሩ ቁሳቁሶች ዛሬ በአብዛኛው በፕላስቲክ እየተተኩ መሆናቸው ተፈላጊነቱን እያጎላው መምጣቱ ተገልጿል፡፡ ዘርፉ ቢስተጓጎል ጉዳቱ ሁሉም ላይ ያርፋል የሚል እምነት ያላቸው የማኅበሩ መሪዎች፣ ይህም ፕላስቲክ የማይነካው ዘርፍ የሌለ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በእርሻና በኮንስትራክሽን፣ በማሸጊያ፣ በመጓጓዣ፣ በቤት ውስጥ መገልገያዎችና የመሳሰሉት በአብዛኛው እየተሠሩ ያሉት ከፕላስቲክ ነው፡፡

መኪኖች፣ ሞተር ሳይክሎችና አውሮፕላኖች ከግማሽ በላይ የሚሆነው አካላቸው ከፕላስቲክና ከጎማ የሚሠራ መሆኑ ዘርፉ ምን ያህል ጠቀሜታ እንዳለው ያመለክታልም ተብሏል፡፡

ብዙዎች የፕላስቲክ ምርት ሲባል የፌስታልና የውኃ መያዣ ምርት አድርገው የሚመለከቱ ቢሆንም፣ ዘርፉ እጅግ ሰፊ የሆነ ሽፋን ያለው መሆኑን የገለጹት አቶ ምንተስኖት፣ በመላው ዓለም ሰዎች የሚለብሷቸው ቲሸርትና ሸሚዝም ሳይቀር ጥጥ ይመስላል እንጂ ብዙ ጊዜ ፖሊስተር ከሚባል የፕላስቲክ ጥሬ ዕቃ የሚሠሩ ናቸው፡፡ በተለይ ጫማዎች ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ከፕላስቲክ የሚሠሩ መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቱ ወንበር፣ ሶፋ፣ አልጋና የመሳሰሉትም አናስተውለው እንጂ የፕላስቲክ ግብዓቶች የሚሠሩ ናቸው በማለት የዚህን ዘርፍ ጠቀሜታ አጉልተዋል፡፡

የፕላስቲክ ጠቀሜታ ከዚህም በላይ የሆኑ ምርቶች የሚገኙበት ሲሆን፣ ከኮንስትራክሽን ዘርፉም በስፋት እየተገባበት ያለው የፕላስቲክ በርና መስኮትም ሌላው ማሳያ ነው ተብሏል፡፡ በኢትዮጵያም በተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የፕላስቲክ ምርቶች መመረት ከጀመሩ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሲሆን፣ በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ የሚባሉ ከ4,500 በላይ አምራቾች እንዳሉ የተገለጸ ሲሆን፣ እነዚህ ማምረቻዎች መስፋፋት ከውጭ ይገቡ የነበሩ የፕላስቲክ ምርቶችን እዚሁ መተካት የቻሉ ሲሆን፣ አሁን የገጠማቸው ችግር ግን ካልተፈታ ለፕላስቲክ ምርቶች ሌላ የውጭ ምንዛሪ ወጪ እንድታወጣ ያስገድዳልና መንግሥት ዘርፉን ይይ የምንለው ለዚህ ጭምር ነው ብለዋል፡፡

የውኃ ፓምፖችና ለመስኖ የሚሆኑ ውኃ ማውረጃዎች ሳይቀሩ የዚህ ዘርፍ ውጤት መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ሳምሶም፣ «ለዚህ ዘርፍ ትኩረት ይሰጥ የምንለው የሚነካው ነገር ብዙ በመሆኑ ነው፤» ይላሉ፡፡

ከዚህ ቀደም ከኬንያ ይመጡ የነበሩ የቤት ውስጥ መገልገያ የፕላስቲክ ምርቶችና ተያያዥ የሆኑ ዕቃዎች አሁን በአገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉን በማስታወስ፣ የዚህ ዘርፍ ጠቀሜታ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት ላይ የሚሠራ መሆኑን የማኅበሩ መሪዎች ተናግረዋል፡፡ ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ የፕላስቲክ ዕቃዎችን ታመጣ የነበረው ከኬንያ ቢሆንም፣ ዛሬ ላይ ግን ምንም ዓይነት የፕላስቲክ ምርት የማይገባው አገር በቀል ኩባንያዎች በመፈጠራቸው ነው፡፡ ከቻይና ይመጡ የነበሩት ጥቂት የማይባሉ የፕላስቲክ ምርቶችንም በአገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉን ከተሰጠው ማብራሪያ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ከማኅበሩ አመራሮች መረዳት እንደተቻለው የፕላስቲክ አምራቾች በቀጥታ የውጭ ምንዛሪ እንዲፈቀድላቸው ማድረግ ለችግሩ አንድ መፍትሔ ነው ብለው ያምናሉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመርያ በአግባቡ መተግበር ቢቻል ደግሞ የተሻለ ሊሆን እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡ አሁን ላይ ብዙዎቹን አምራቾች ከደረጃ በታች እንዲያመርቱ ካስገደዱ ምክንያቶች አንዱ፣ ከዚሁ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ካወጣው መመርያ ጋር ይያያዛል ተብሏል፡፡

ይህም በመመርያው መሠረት ላኪዎች ከሚያገኙ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ ዕቃ የሚያስመጡት ከ70 በመቶ ወደ 30 በመቶ መውረዱ እንደሆነ አቶ ሳምሶም ገልጸዋል፡፡ «ኤክስፖርተሮች 70 በመቶው በሚፈቀድላቸው ጊዜ የእኛን ጥሬ ዕቃ አስመጥተው ገበያ ላይ ጥሬ ዕቃውን ማግኘት ይቻል ነበር ያሉት አቶ ሳምሶም፣ ከውጭ ጥሬ ዕቃ ያስመጡበት የነበረው የውጭ ምንዛሪ ሲቀንስ እነሱም የእኛን ጥሬ ዕቃ ማምጣት በማቆማቸው በተወሰነ ደረጃ ይመረቱ የነበረውን ምርት እስከናካቴው እያስቀረው ስለሆነ የብሔራዊ ባንክ መመርያም መታየት እንደሚኖርበት ጠቁመዋል፡፡

ስለዚህ የብሔራዊ ባንክ መመርያ በአግባቡ ካለመተግሩም በላይ፣ እነሱ በሦስተኛ ወገን ያገኙት የነበረውን ጥሬ ዕቃ ይህ መመርያ ተፅዕኖ እንዳሳደረገበት ያልሸሸጉት የአቶ ሳምሶም ዘርፉን መንግሥት ይመልከተው የሚል ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://ethiopianreporter.com/article/25092

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዘካ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የማስተዋወቅ ንቅናቄ ጀመረ

ባንኩ የሺሪዓ መርህን መሰረት ያደረገ የተሟላ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

ዘካ ከእስልምና እምነት መሰረቶች አንዱ ሲሆን አቅም ያላቸው ግለሰቦች ካፈሩት ሃብት የተወሰነውን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት እምነቱ ዘካ እንዲቀበሉ ለፈቀደላቸው ግለሰቦች የሚሰጥ የግዴታ ክፍያ ነው፡፡

የሃይማኖት አባቶች፣ የባንኩ አመራሮች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት የዘካ ተቀማጭ ሂሳብን የማስተዋወቅ ንቅናቄ ተጀምሯል።

ብዙም ያልተለመደው የዘካ ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት በሀገሪቱ ጥሩ እንቅስቃሴ እንዳለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዝዳንት አቤ ሳኖ ገልፀዋል።

ባንኩ የሺሪአ ኮሚቴ ከማቋቋም ጀምሮ በሁሉም ባንኮቹ የሲቢኢ ኑር አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን ለዘካ የሂሳብ አገልግሎትም ባንኩ 109 ቅርንጫፎች እንዳሉት ፕሬዝዳንቱ ተናግረዋል።

የታላቁ የረመዳን የፆም ወር ዋዜማን ያስታወሱት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፕሬዝዳንት አቤ ሳኖ እና የባንኩ የሲቢኢ ኑሮ ምክትል ፕሬዝዳንት ኑር ሁሴን የዛካ ሂሳብ አገልግሎትን በይፋ አስተዋውቀዋል።

የባንኩ የሺሪዓ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ መሀመድ ሀሚዲን (ዶ/ር) ዘካ በመካከላችን መተሳሰብንና መተጋገዝን የምናጎለብትበት መልካም እሴታችን በመሆኑ ሕዝበ ሙስሊሙ ሊተገብረው ይገባል ብለዋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://waltainfo.com/am/የኢትዮጵያ-ንግድ-ባንክ-የዘካ-ከወለድ-ነፃ/

# ዘመን ባንክ የማስተር ካርድ የክፍያ ስርዓት መተግበር የሚያስችለውን ስምምነት አደረገ




ዘመን ባንክ ኤም ፒ ጂ ኤስ የተባለ የማስተር ካርድ ስርዓትን በማስጀመር ክፍያዎችን በቀጥታ መክፈል የሚያስችል ቴክኖሎጂን አስተዋውቋል።

ይህንን ቴክኖሎጂ ያስተዋወቀው ከማስተር ካርድ ጋር በመሆን ነው።

ይህ የክፍያ ስርዓትም ለአየር መንገድ እንዲሁም ለሆቴሎች ቅድሚያ አገልግሎት ክፍያ መፈጸም የሚያስችል ነው ተብሏል።

ከዚህ በተጨማሪም የኦንላየን ግብይቶችን በቀጥታ መክፈል የሚያስችል ነው።

ይህ የክፍያ ስርዓትም በኢትዮጵያ ብርም መገበያየት የሚያስችልና የቀጥታ ክፍያ ንክኪን የሚቀንስ ነው።

ኢኮሜርስ አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተስፋፋ የመጣ ከመሆኑ አንጻር እንዲህ አይነት ቴክኖሎጂ ግብይቱን በአንድ ቦታ በመጨረስ እንዲቀላጠፍ ያደርጋል።

ለተጨማሪ መረጃ፡

https://www.fanabc.com/ዘመን-ባንክ-የማስተር-ካርድ-የክፍያ-ሲስተ/

## የግል አየር መንገዶች አድሎ እየተፈጸመባቸው መሆኑን ተናገሩ

የግል አየር መንገዶች ኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር እንዲተዳደር በመደረጉ፣ እኩል አገልግሎት እንዳናገኝ አድርጎናል አሉ።

የኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝ ከአራት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር እንዲተዳደር መደረጉ የሚታወስ ሲሆን፣ የግል አየር መንገዶችም የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች በዚሁ መሠረት እንዲያገኙ ተወስኗል። ነገር ግን የግል አየር መንገዶች አገልግሎቶችን ተፎካካሪያቸው ከሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንዲጠይቁ መደረጋቸውን ትክክል አይደለም ሲሉ ተቃውመዋል።

የአቢሲኒያ የበረራ አገልግሎትና አቪዬሽን አካዳሚ ባለቤትና ማኔጂንግ ዳይሬክተር ካፒቴን ሰለሞን ግዛው፣ ከኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝ ሲያገኟቸው የነበሩ አገልግሎቶችን በአሁኑ ወቅት በተገቢው መንገድ እያገኙ እንዳልሆነ ተናግረዋል። በተለይም ለግል አየር መንገዶች ትልቅ ፈተና የሆነው የማረፊያ ቦታ ጥያቄ እስካሁን ድረስ አለመመለሱን ገልጸዋል።

በዚህም ምክንያት ያሏቸውን 14 ያህል አውሮፕላኖች በሙሉ አቅም ለማሠራት መቸገራቸውን ተናግረው ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ጥያቄዎቻችን ሊመለሱ ይገባል ብለዋል። ኢንተርፕራይዙን የሚያስተዳድረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፉክክሩን በመፍራት የሚቀርቡለትን ጥያቄዎች እያስተናገደ አይደለም ብለዋል።

ሌላው ችግር የጥገና ቦታ እጥረት ሲሆን ይህም ለተጨማሪ ወጪ እየዳረጋቸው እንደሚገኝ ካፒቴን ሰለሞን አስረድተው፣ የጥገናና ዕድሳት አገልግሎት የሚያገኙት ኬንያ፣ ናይሮቢ በመሄድ እንደሆነ ይገልጻሉ። «ለጥገናና ለዕድሳት አውሮፕላኖችን ወደ ኬንያ መላካችን በአንድ አውሮፕላን ከ10,000 ዶላር በላይ ተጨማሪ ገንዘብ ወጪ እንድናደርግ አስገድዶናል፤» ብለዋል። «ይህም በተለይ በኮቪድና በሌሎች አገራዊ ችግሮች የተጎዳውን የግል አየር መንገዶች ቢዝነስ እንዳያገግም እያደረገው ነው፤» በማለት ትክክለኛ አገልግሎት እንዲገኝ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ሊወጣ ይገባል ብለዋል።

በአቪዬሽን ዘርፍ በተለይም ለግል አየር መንገዶች ላይ በቂ ትኩረት እንዳልተሰጠ የሚገልጹት ካፒቴን ሰለሞን፣ ለዘርፉ በቂ ድጋፍ ለማድረግ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ደረጃ የሲቪል አቪዬሽን አማካሪ እንዲቋቋም ጠይቀዋል።

የአኳሪየስ አቪዬሽን ማኔጂንግ ዳይሬክተር ወ/ሮ ፍሬሕይወት ተሰማ በበኩላቸው፣ የማረፊያ ቦታ ከፍተኛ ችግር በመሆኑ በውጭ ምንዛሪ ለሚከፈል ተጨማሪ ወጪ መዳረጋቸውን ተናግረዋል። በዚህም መሠረት በመንግሥት የማይቻል ከሆነ የግል ባለሀብቶች የማረፊያ ቦታዎችን እንዲገነቡ ምክረ ሐሳብ መቅረቡን ይገልጻሉ። «የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተመሳሳይ ሥራ ውስጥ ሆኖ ኤርፖርትን ማስተዳደር የለበትም፣ መመራት ያለበት በመንግሥት ነው፤» ብለዋል።

የግል አየር መንገዶቹ ባነሷቸው ጥያቄዎች ላይ ለሪፖርተር ምላሽ የሰጡት የሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የኢኮኖሚክ ሬጉሌሽንና ስትራቴጂክ አመራር ዳይሬክተር አቶ እንደሻው ይገዙ፣ በአገልግሎቶቹ ላይ የሚነሱት ጥያቄዎች ኢንተርፕራይዙ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር በመካተቱ የመጡ አይደሉም ይላሉ። ኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር የተካተተው ሁለት ዓመታት ከፈጀ ጥናት በኋላ መሆኑን ገልጸው፣ ኤርፖርቱ በሚፈለገው ደረጃ ባለማደጉና ማሻሻያ ለማምጣት በማሰብ የተላለፈ ውሳኔ መሆኑን አስረድተዋል።

የማረፊያም ይሁን የጥገና አገልግሎት ማግኘት ያልተቻለው በቂ መሠረተ ልማት ባለመኖሩ መሆኑን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ቦታ ለመጠቀም በቂ ቦታ ማግኘት አለመቻሉን ተናግረዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማረፊያ፣ ለሥልጠናና ለሌሎች ጉዳዮች ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ለመደበኛ በረራዎች ከአየር መንገዱ አውሮፕላኖች በተጨማሪ ለ13 የውጭ አየር መንገዶች አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን አብራርተዋል።

«በዚህም ምክንያት ለግል አየር መንገዶች የማረፊያና የጥገና ቦታ ለመገንባት የሚቻልበት መንገድ ጥናት እየተደረገበት ነው፤» ያሉት ዳይሬክተሩ፣ «በግል ባለሀብቶች ለማልማት የሚቻል በመሆኑ ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ ቦታዎች መገንባት እንደሚቻል ለመለየት እየሠራን ነው፤» ብለዋል።

በተጨማሪም ሰባት ዓመታት የፈጀውና እስካሁን ያልፀደቀው የአቪዬሽን ፖሊሲ በተያዘው ዓመት እንደሚፀድቅ ይጠበቃል ያሉት አቶ እንደሻው፣ በተለይ በግል አየር መንገዶች የሚነሱ ጥያቄዎችን ይፈታል ሲሉ አስረድተዋል።

ለተጨማሪ መረጃ:

https://www.ethiopianreporter.com/article/25058

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሾመ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አቶ መስፍን ጣሰውን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አድርጎ መሾሙን አስታወቀ፡፡

አቶ መስፍን በቶጎ የኤስካይ (ASKY) ማኔጂንግ ዳይረክተር በመሆን እየሰሩ ነበር፡፡ አቶ መስፍን በአየር መንገዱ ለ38 ዓመታት በተለያዩ ኃላፊነቶች ሲያገለግሉ እነደነበር ተጠቁሟል፡፡

አየር መንገዱ የቦርድ አባላቱን በአዲስ መልክ ያዋቀረ ሲሆን አቶ ግርማ ዋቄ የቦርድ ሰብሳቢ፣ የንግድ ባነክ ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑትን አቶ ተክለወልድ አጥናፉ፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነትዋና ዳይሬክተር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዢ ሌተናል ጀነራል ይልማ መርዳሳ፣ የኖክ ባለድርሻና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ጥላሁንና አቶ ረታና አቶ አለማየሁ አባላት ሆነዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተወልደ ገብረማርያም ባጋጠማቸው የጤና እክል ምክንያት ከኃላፊነታቸው በፈቃዳቸው መልቀቃቸውን በትላንትናው እለት መግለጻችን ይታወሳል።

ለተጨማሪ መረጃ:

https://www.ethiopianreporter.com/article/25047

## የጭነት አግልግሎትን ያቀላጥፋል ተብሎ የታመነለት ‘ዚትራክ’ የተሰኘ መተግበሪያ ይፋ ሆነ

በኢትዮጵያ የጭነት አግልግሎትን ያቀላጥፋል የተባለ ‘ዚትራክ’ የተሰኘ መተግበሪያ ይፋ ሆነ፡፡

መተግበሪያው የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር  በለጠ ሞላ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ሹመቴ ግዛውእና የዚ ትራክ የትራንስፖርት አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ዋና ስራ አስኪያጅ ዮዲት ደነቀው በተገኙበት ነውይፋ የተደረገው።

መተግበሪያው ሙሉ ለሙሉ በኢትዮጵያውያን የለማ ሲሆን፥ በስልክና ኮምፒውተር ላይ በመጫን የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማቀላጠፍ የሚያግዝ ነው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶክተር በለጠ ሞላ የኤሌክትሮኒክ ንግድ በኢትዮጵያ በተሟላ ደረጃ ለመተግበር እንደ ‘ዚትራክ’ ያሉ መተግበሪያዎች ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ብለዋል።

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉትን ችግሮች በአሰራር፣ በብቁ የሰው ሃይል፣ በአደረጃጀትና በቴክኖሎጂ መቅረፍ ከተቻለ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የሎጂስቲክስ ማዕከል ማድረግ እንደሚቻልም ተናግረዋል።

በጭነት አገልግሎት ለተሰማሩ አስተላላፊዎች፣ አሽከርካሪዎችና ደንበኞች ስራዎቻቸውን ያቀላጥፋል የተባለው መተግበሪያው ወደ ስራ ለመግባት ዝግጅቱን ማጠናቀቁን በስነ ስርዓቱ ላይ ተገልጿል።

‘ዚትራክ’ ሶስት መተግብሪያዎችን የያዘ ሲሆን፥ እርስ በእርሳቸው የሚናበቡ የጭነት አገልግሎት ሰጪውንና ደንበኛውን የሚያገናኙ፣ ጭነቱ የደረሰበትን ቦታና የሚደርስበትን ጊዜ ለመከታተል የሚያስችሉ ናቸውም ነው የተባለው።

ለተጨማሪ መረጃ:

https://www.fanabc.com/የጭነት-አግልግሎትን-ያቀላጥፋል-ተብሎ-የ/

## የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚመሩበት አዲሱ መመርያ ከአምስት ዓመት በኋላ አስገዳጅ ይሆናል ተባለ

የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚመሩበት አዲሱ የኮንስትራክሽን ኮድ ከአምስት ዓመታት በኋላ በአስገዳጅነት እንደሚተገበር፣ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

አዲሱ ኮድ የኮንትራክተሮችን፣ የአሠሪዎችን፣ የሠራተኞችንና የሁሉንም የፕሮጀክት ተሳታፊ አካላት መብትና ግዴታ የሚወስን ሲሆን፣ በሁሉም ዘርፎች ላይ የመተግበሪያ ደረጃዎች ተዘጋጅተውለታል።

አዲሱ ኮድ ለኮንትራክተሮችና ለአሠሪዎች የተዘጋጁ 19 የሥራ ስታንዳርዶች (ማኑዋሎች) እንዳሉት፣ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት የሥርዓት ማሻሻያ ዳይሬክተር አቶ አበራ አውግቸው ለሪፖርተር ተናግረዋል።

‹‹ማኑዋሎቹ ከፕሮጀክት ዕቅድ እስከ ማጠናቀቂያ ድረስ ያለውን አሠራር በግልጽ ለማሳየት የሚያስችሉ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው፤›› ብለው፣ የሠራተኞች ደኅንነት በኮዱ ውስጥ ተፈጻሚነት ካላቸው ዋና ዋና መመርያዎች ውስጥ አንዱ መሆኑን፣ የኮንስትራክሽን ዘርፉን እየተፈታተኑ ያሉት የወጪ አስተዳደር፣ ግዥ፣ ኮሙዩኒኬሽን፣ የግንባታ ጊዜና ሌሎች መመርያዎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

ከሁለት ሚሊዮን በላይ ሠራተኞችን የሚያሳትፈው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለሠራተኞች የሥራ ቦታ ደኅንነት ሥጋት ያለበት ሲሆን፣ አስገዳጅ የደኅንነት ሥርዓት አለመኖሩ ለኮንትራክተሮችም ሆነ ለሠራተኞቹ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ነው። በዚህም መሠረት አዲሱ ኮድ የግንባታ ፕሮጀክቶች ሲቀርቡ በዋጋ ዝርዝራቸው ውስጥ ለደኅንነት የሚመደብ በጀት በአስገዳጅነት ይጠየቃል። ‹‹ተቋራጮች ለደኅንነት ምንም ዓይነት በጀት ስለሌላቸው ሠራተኞቹ በአደጋ ጊዜ ዋስትና አይኖራቸውም፤›› ያሉት አቶ አበራ፣ አሠሪዎቹ የደኅንነት ወጪን የመቀበል ግዴታ አለባቸው ብለዋል።

‹‹ኮዱ እንደታቀደው ከአምስት ዓመታት በኋላ አስገዳጅ ይሆናል። ነገር ግን አሁን ለኮንትራክተሮችና ለአሠሪዎች እየተሰጠ የሚገኘው ማኑዋል በተሻለ ሁኔታ የአስገዳጅነት ጊዜው ወደ ሦስት ዓመት ዝቅ ይላል፤›› በማለት ገልጸዋል።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው አንዱ ፈተና የሠራተኞችን ደኅንነት አለመጠበቅ በመሆኑ፣ አዲሱ ኮድ ይህንን ችግር የሚቀርፍ እንደሚሆን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ማኅበር ፕሬዚዳንት ግርማ ኃይለ ማሪያም (ኢንጂነር) ገልጸዋል።

አሠሪውም ሆነ ኮንትራክተሩ ለደኅንነት ቅድሚያ በመስጠት በራስ ላይ የሚኖርን ሥጋት መቀነስ የሚያስችል አሠራር እንደሚሆን የገለጹት ግርማ (ኢንጅነር)፣ በደኅንነት ላይ የሚሠሩ በቂ ባለሙያዎች ባለመኖራቸው ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ጋር በመሆን ሥልጠና ሊሰጡ ማቀዳቸውን ተናግረዋል።

ሌላው የኮንስትራክሽን ዘርፉ ፈተና የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ንረት ሲሆን፣ ይህም ፕሮጀክቶች በታሰበላቸው ጊዜና በጀት እንዳይጠናቀቁ በማድረግ በአሠሪዎችና በኮንትራክተሮች መካከል አለመግባባት እንዲፈጠርና ፕሮጀክቶችም እንዲቋረጡ እያደረገ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ኮንትራክተሮች የፕሮጀክቶችን ዋጋ ሲያወጡ በቂ ግምገማ በማድረግና የሚኖረውን የዋጋ ንረት ግምት ውስጥ በማስገባት ኪሳራና አለመግባባትን የሚያስቀሩ ሳይንሳዊ መንገዶችን እንዲከተሉ የሚያደርግ እንደሚሆን አቶ አበራ አስረድተዋል።

ለተጨማሪ መረጃ:

https://www.ethiopianreporter.com/article/24931

ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ

አዘጋጅ፡- ዮሴፍ ተሾመ


አድራሻ፡-

ስልክ-፡- +251-115-54-09-93

ፋክስ፡-+251-011-5517699

ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

Facebook: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Twitter: https://twitter.com/EthiopiaChamber

Telegram: t.me/ethiopiachamber


## ECCSA Resource Center

Ethiopian Chamber of Commerce & Sectoral Associations (ECCSA) Resource Center has stated giving service to member. The center is located at the head quarter of ECCSA.

It is a unit dedicated to serve the business community, its members and staffs with a range of timely and cost-effective information services which will enhance the decision-making process and competitiveness of the chamber system management and the business community.

It is also a WTO (World Trade Organization) Reference Center for the private sector, to enable business community to access online trade data and WTO-related documents on a continuous basis, to help identify market niches for the export of their products and services.

The center works on the principle of the 5Rs: providing the Right information to the Right person at the Right time in the Right quantity and Right quality.

The Center's Services

Reference, Resources Loan & Interlibrary Loan Services

Internet & Electronic Resource Services

Support on information searching

Reprographic Service

Advising users on reference materials available in resource center.

Types of Materials in the Center

Books, Periodicals, Journals, Magazines

Audio and Video CD collections

E-Books & Publications

Business & Economic Statistics & Databases

Access to international organization's online information (WTO, ITC, UNCTAD, World Bank, PACCI, WCO, etc.)

For further information:

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations

ECCSA Resource & WTO Reference Center

Mexico Square, ECCSA Building

Ground Office , Room No. 13/14

Open to public Monday-Friday from 2:30 am to 5:00 pm

Tel: 251-115514005

Mob. 0966038499

Fax: 251-115517699

# የግልግል አገልግሎት



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 341/95 አንቀጽ 5(6) መሰረት በንግድ ማህበረሰቡ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን እንዲፈታ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሰረት አለመግባባቶችን በፈጣን እና ሚስጥራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እንዲፈታ ከማድረጉም በላይ ለባለ ጉዳዮች አመቺ እንዲሆን ቅዳሜንም ጨምሮ ዓመቱን ሙሉ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑን የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆኑ ስንጠይቅ የንግድ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ያለንን ቁርጠኝነት በመግለጽ ነዉ፡፡

ለበለጠ መረጃ ፡- ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘዉ የንግድ ምክር ቤት ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 15 በአካል በመቅረብ

ወይም

በስልክ ቁጥር +251 115 311015 በመደወል ማነጋገር ትችላላችሁ፡፡

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት**
**የግልግል ማዕከል**